የፌደራል የሥነምግባር እና
የፀረ-ሙስና ኮሚሽን

FEDERAL ETHICS AND
ANTI-CORRUPTION COMMISSION

የትምህርት ሴክተር የሙስና ስጋት ጥናት ሪፖርት

አዘጋጆች፡

1. ዶ/ር አራጋው እሸቴ
2. ዶ/ር ሞላ አለማየሁ
3. ዶ/ር ዳርእስከዳር ታዬ
4. አበበ ይሄይስ

ሰኔ/2014

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

ማውጫ

የጥናቱ አጭር ማጠቃለያ (Executive Summary) 3
ክፍል 1፡ መግቢያ 5
1.1. የጥናቱ ዳራ (Background of the study) 5
1.2. የጥናቱ መነሻ ችግሮች (Statement of the Problem) 6
1.3. የጥናቱ ዓላማ (Objective of the Study) 6
1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት (Significance of the Study) 7
1.5. የጥናቱ ውስንነት (Limitation of the study) 7
ክፍል 2፡ የጥናቱ ስነ ዘዴ 7
2.1. የጥናቱ ቦታ (Study Area) 7
2.2. የጥናቱ ንድፈ-ሃሳብ (Research design) 7
2.3. የጥናቱ ተሳታፊዎች (Study Participants) 7
2.4. የናሙና አመራረጥ ስልት (sampling techniques) 8
2.4. መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች (Data collection methods) 8
ደረጃ 1፡ የዝግጅት ምዕራፍ (ተሳታፊዎችን መለየት) 8
ደረጃ 2፡ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስና ስጋቶችን መለየት 8
ደረጃ 3፡ የሙስና ስጋቶችን መተንተን 9
2.5. የመረጃ ትንተና ዘዴ (Methods of Data Analysis) 10
ደረጃ 4፡ የሙስና ስጋቶችን መገምገም/መመዘን 10
ደረጃ 5፡ የሙስና ስጋቶችን ለማከም ምክረ ሃሳብ ማቅረብ 11
ክፍል 3፡ የሙስና ስጋት ትንተና 12
3.1. በትምህርት ዘርፍ ላይ የሚታዩ የሙስና ስጋቶች 12
3.2. ለሙስና መከሰት መነሻ ምክንያት ተደርገው የሚወሰዱ ጉዳች 15
3.3. ከሙስና ስጋት አንፃር የትምህርት ተቋማት ያሉበት ሁኔታ 16
3.3.1. በትምህርት ተቋማት ያለው የአመራር ሁኔታ 16
3.3.2. በትምህርት ተቋማት ውስጥ ሙስናን የሚመለከቱ አሰራሮች፣ ደንቦችና መመሪያዎች 17
ክፍል 4፡ የሙስና ስጋት ምዘናና ግምገማ 21
4.1. በሁሉም የትምህርት ተቋማት የሙስና ስጋት ምዘና 21
4.2. ለሙስና ተጋላጭ ተደርገው በሚወሰዱ የስራ ክፍሎች ላይ የስጋት ምዘና 25
4.3. በትምህርት ተቋማት ውስጥ በሚገኙ ግዥ ክፍሎች ውስጥ የስጋት ምዘና 28
4.4. በፈቃድ አሰጣጥና ስረዛ የስራ ሂደቶች ዉስጥ የሙስና ስጋት ምዘና 31
4.5. በህንፃ ግንባታና ዕድሳት ወቅት የሚከሰቱ የሙስና ተጋላጭነትና ስጋት ትንተና እና የተጽዕኖ ደረጃ 33
ክፍል 5፡ ማጠቃለያና ምክረ-ሃሳብ 36
ማጣቀሻዎች 39
አባሪ 40

የጥናቱ አጭር ማጠቃለያ (Executive Summary)

ይህ ጥናት የትምህርት ተቋማት በሚሰጡት አገልግሎት የሙስና ሥጋት የሆኑ አሰራሮችን መለየት፣ ደረጃ መስጠት፣ ባህሪያትን መፈተሽ፣ የሚከሰትባቸውን የሥራ ክፍሎች፣ የሙስና ምንጭና የሚያደርሰውን አሉታዊ ተፅእኖ በማወቅ የመፍትሔ ሐሳብ ለመጠቆም ታስቦ የተካሄደ ጥናት ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዋና አላማ በትምህርት ሴክተር ውስጥ ያለውን የሙስና ስጋት በመለየትና በመመዘን የመፍትሄ ምክረ-ሃሳብ መስጠት ነው፡፡ ጥናቱ የተካሄደው በፌድራል የትምህርት ተቋማትና በሁለት ክልሎች እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ የተመረጡ የትምህርት ተቋማት ውስጥ ነው፡፡ የጥናቱን አላማ ለማሳካት ቅይጥ የምርምር ስልት ተግባራዊ የሆነ ሲሆን 1065 መጠይቅና ቃለመጠይቅ ከተቋማቱ ሰራተኞችና አመራሮች ተሰብስቧል፡፡ በተጨማሪም የሃሳብ ማጎልበት (brainstorm) እና የሰነድ ትንተና ለጥናቱ ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

በሙስና ስጋት ጥናት ውስጥ የስጋት አይነቶችን መለየት የመጀመሪያው ስራ እንደመሆኑ መጠን በዚህ ጥናትም በትምህርት ሴክተር ውስጥ የሚታዩ ስጋቶች ተለይተው ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ስጋቶች በሁለት ደረጃ የታዩ ሲሆን የመጀመሪያው በተቋማቱ የአስተዳደርና ፋይናንስ ክፍሎች ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ ስጋቶች ናቸው፡፡ በፋይናንስ፣ በግዥ፣ በንብረት አስተዳደርና በሰው ሃብት ለማትና አስተዳደር የሚከሰቱ ስጋቶች በዝርዝር ተለይተው ቀርበዋል፡፡ በመቀጠል ደግሞ ከመማር-ማስተማርና ስልጠና ጋር በቀጥታ የተያያዙ ስጋቶች በተለያየ እይታ ቀርበዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል የመጀመሪያው ከመምህራን ወይም አሰልጣኞች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ስጋቶች ናቸው፡፡ በመቀጠል የቀረበው ከሃሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ የስጋት አይነቶች ናቸው፡፡ በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች ውስጥ በሚገኙ ሬጅስትራር ፅህፈትቤቶች ውስጥ የሚታዩ ስጋቶችም በልዩ ሁኔታ የሚታዩ ናቸው፡፡ እነዚህን የስጋት አይነቶች ከመዘርዘር ባለፈ ለስጋቶቹ መነሻ የሆኑ ምክንያቶችም በተያያዥነት አብረው ቀርበዋል፡፡ ስጋቶቹ በትምህርት ተቋማት እንዳይከሰቱ ለማድረግ ወይም ከተከሰቱ በኋላ የእርምት ርምጃ ለመውሰድ የሚቻለው ከሙስና አንፃር ተቋማቱ ያሉበት ሁኔታ ሲዳሰስ በመሆኑ በጥናቱ የተካተቱ የትምህርት ተቋማት ያሉበትን የአመራር ሁኔታና የዘረጉትን የአሰራር ስርዓት ለማየት ጥረት ተደርጓል፡፡

በተለያዩ የትንተና ዘዴዎች ተለይተው የወጡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ከሆነ ከአንድ እስከ አስራ ዘጠኝ ድረስ በቅደም ተከተል ሊቀመጡ የሚችሉ የሙስና አይነቶች ሲኖሩ ከእነዚህም መካከል የመከሰት ዕድላቸው ከፍተኛ ከሆኑት የሙስና ስጋቶች ዉስጥ ቀዳሚዎቹ አራቱ የሚከተሉት ናቸው፡- (1) የመምህራን በተደጋጋሚ ክፍል አለመግባት፣ (2) ህገወጥ ቅጥር፣ ዝዉዉርና ደረጃ ዕድገት፣ (3) የአሰራር ግልጥነት መጓደል፣ እና (4) ግዥዎች ህግና ደንብን ተከትለዉ አለመከናዎን ናቸው፡፡ በዝርዝር ከተለዩ የሙስና አይነቶች መካከል ሁሉም ተመሳሳይ ጉዳት ያደርሳሉ ተብሎ

ስለማይታሰብ ሁሉንም በደረጃ ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ ከዚህ አንፃር ቢከሰቱ የበለጠ ጉዳት ሊያደርሱ ከሚችሉ የሙስና አይነቶች መካከል ቀዳሚዎቹ አራቱ፡- (1) የመምህራን በተደጋጋሚ ክፍል አለመግባት፣ (2) ህገወጥ ቅጥር፣ ዝዉዉርና የደረጃ ዕድገት፣ (3) በአመራሩ የሚከናወን ስርቆት፣ እና (4) ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ መስጠት ናቸው፡፡

የመከሰት እድልን ከሚያደርሰው ተፅዕኖ ጋር በማዛመድ በተሰራው የሙስና የስጋት ደረጃ ሁሉም የሙስና አይነቶች በሶስት ደረጃ ማለትም አነስተኛ፣ መካከለኛና ከባድ በሚል ተከፋፍለዋል፡፡ ከባድ በሚል የተለዩ የሙስና አይነቶች ልዩ ትኩረት የሚፈልጉና ሁሉም የትምህርት ተቋማት ቅድሚያ ሰጥተው መፍትሄ ሊፈልጉላቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ከባድ በሚል የተለዩ የሙስና አይነቶች የመምህራን በተደጋጋሚ ክፍል አለመግባት፣ ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ መስጠት፣ በአመራሩ የሚከናወን ስርቆት፣ ህገወጥ ቅጥር፣ ዝዉዉርና ደረጃ ዕድገት፣ ግዥዎች ህግና ደንብን ተከትለዉ አለመከናዎን፣ የመረጃና ማስረጃ ማጭበርበር፣ እና የአሰራር ግልጥነት መጓደል ናቸው፡፡

የስጋት ትንተናና ምዘና ስራው የበለጠ የችግሩን ይዘት ማሳየት ይችል ዘንድ በተመረጡ የስራ ዘርፎች ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ስጋቶች ተለይተው የስጋት ምዘና ተከናውኗል፡፡ ከእነዚህ መካከል ለሙስና ተጋላጭ ተደርገው በሚወሰዱ ስምንት የስራ ክፍሎችን በመለየት የትኛው ክፍል ልዩ ትኩረት እንደሚፈልግ በተደረገው ልየታ መሰረት ግዥ ክፍል፣ የሰው ሃብት ልማትና አስተዳደር እና ሬጂስትራር ተለይተው ወጥተዋል፡፡ በመቀጠል በግዥ ክፍል ውስጥ ከሚከናዎኑ ተግባራት መካከል በየትኛው የበለጠ የሙስና ስጋት እንደሚታይ በተደረገው ጥረት ስጋቶቹ ጎልተው የሚታዩት በግዥ ዝግጅት ወቅት፣ በግዥ ሰነድ ዝግጅትና የጨረታ ሰነድ ግምገማ ወቅት መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በፈቃድ አሰጣጥ ላይ የሚታዩ ችገሮችን በተመለከተ በተደረገው ትንተና ከባድ ስጋት አለመኖሩን ለማየት ተችሏል፡፡ በመጨረሻም በህንፃ ግንባታና ዕድሳት ወቅት ሊከሰቱ ከሚችሉ ስጋቶች መካከል በግንባታ ስራዎች ቁጥጥርና ክትትል ጊዜ ጥራቱን ያልጠበቀ ገንባታ እንዲካሄድ መፍቀድና በህንፃ ርክክብ ጊዜ ጥራቱ የተጓደለ ህንፃ መረከብ እንደ ከባድ የሙስና ስጋት ተወስደዋል፡፡

ክፍል 1፡ መግቢያ

የፌዴራል የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሙስና በተለያዩ የመንግስትና የግል ተቋማት ላይ ያለበትን ሁኔታ ለመረዳት እንዲያግዘው የሙስና ስጋት ጥናት እያካሄደ ይገኛል፡፡ ጥናቱ በሶስት ሴክተሮች ማለትም በገቢዎችና ጉምሩክ፣ በፍርድቤቶችና በትምህርት ሴክተር ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ይህ ጥናትም በትምህርት ሴክተር ላይ ያለውን የሙስና ስጋት የሚያሳይ ነው፡፡ የትምህርት ሴክተሩ ሀገራችን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ እንድትሰለፍ ለማድረግ አጠቃላይ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ፣ ትምህርትና ስልጠና እንዲሁም ከፍተኛ ትምህርት ጉልህ ሚና አላቸው፡፡ በመሆኑም ትምህርትን በፍትሀዊነትና በጥራት ተደራሽ ለማድረግ በትምህርት ተቋማት ከሙስና ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን መለየትና አስፈላጊውን የመፍትሄ ርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡ በትምህርት ሴክተሩ ያሉ ችግሮችን ትኩረት ሰጥቶ መለየትና የተሰጠውን ተግባራት በአግባቡ በማከናወን የተመደበለትን ከፍተኛ ሀብት በአግባቡ ለታለመለት አላማ ማዋል ካልተቻለ ሀገሪቱ ልትደርስበት ያሰበችውን ራዕይ ለማሳካት ተግዳሮት ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህም በላይ ዜጎች በድህነት አረንቋ ውስጥ እንዲኖሩ በማድረግ፣ የትምህርት ሴክተሩ ለሀገሪቱ ማበርከት የሚገባውን አስተዋጽኦ በማደናቀፍና በትምህርት ዘርፉ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዲያሳድር በማድረግና በሀገሪቱ ማህበራዊ ዘርፍ ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት ስለሚያደርስ ሙስናንና ብልሹ አሰራሮችን ለማስወገድ ሰፊ ስራዎችን መስራት ይገባል፡፡

ሙስና በሃገር ሁለንተናዊ እድገት ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተፅእኖ በማስከተል ሃገር እንደሃገር በማይቀጥልበት ደረጃ ለማድረስ የሚያስችል እና ተቋማትን የማፍረስ አደጋ ሊያስከትል የሚችል፤ ተለዋዋጭነት ባህሪ ያለው አደገኛ የሆነ የወንጀል አይነት ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ ሃገራት ይህን የተለዋዋጭነት ባህሪ እያሳየ ያለውን የወንጀል ዓይነት ሊመጥን የሚችል የመከላከያ ስልት በመንደፍ ስራ ላይ ለማዋል ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

1.1. የጥናቱ ዳራ (Background of the study)

በትምህርት ዘርፍ የሚስተዋለው ሙስና ትርጉም “የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን ስልታዊ በሆነ መንገድ ለግል ጥቅም ማዋል፣ በትምህርታዊ ዕቃዎችና አገልግሎቶች፣ ተደራሽነት፣ ፍትሃዊነት፣አቅርቦትና ጥራት ላይ ያለው ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው” (ሃላክ እና ፖይሰን፣ 2002 እኤአ)፡፡ ሙስና ሀገራት ለእድገት የሚያደርጉትን ጉዞ በማቀጨጭ እና በማሽመድመድ ዜጎችን ለእንግልትና የሚፈልጉትን አገልግሎት እንዳያገኙ ከማድረግም ባሻገር ለሰላም ማጣትና ለስደት እንዲዳረጉ ከሚያደርጉ መንስኤዎች አንዱ እና ዋነኛው ነው፡፡ “ዜጎች በሃገራቸው የኢኮኖሚ እድገት ያመጣውን ትሩፋት የመጋራትና በመንግስት ገንዘብ የሚሰጡ ማህበራዊ አገልግሎቶችን የማግኘት መብት እንዳላቸው በተለያዩ ሃገራት የሚደነገጉ ህጎችና ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ባላቸው የመብት ድንጋጌ ስምምነቶች ይጠቀሳሉ” (የአለም ባንክ 2014 እኤአ)፡፡ በማህበራዊ ዘርፍ ሥር ከሚገኙ ተቋማት መካከል የጤና ሚኒስቴር፣ የትምህርት ሚኒስቴር፣ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስተር፣ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር እና ለሚኒስቴር መ/ቤቶቹ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጠሪ የሆኑ ተቋማት፣ የኢትዮጵያ የምግብና መድሃኒት ባለስልጣን፣ የመንግሥት እና የግል ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ሌሎች መሰል ተቋማት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በትምህርት ሴክተሩ የሚሰጡ

አገልግሎቶችን በጥራት፣ፍትሃዊና ተደራሽ በሆነ መልኩ ለዜጎች ለማዳረስ በዚህ ዘርፍ ያለውን ሙስና እና ብልሹ አሰራር መከላከል ግድ ይላል፡፡

ሙስና በኢትዮጵያ አንዱ እና ትልቁ ችግር ሲሆን ይበልጥ ይህ ችግር ከሚንፀባረቅባቸው ዘርፎች መካከል በትምህርት ተቋማት ዉስጥ የሚሰሡጡ አገልግሎቶች እንደሆኑ ከዚህ በፊት በተካሄዱ ጥናቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው (Kilimanjaro International, 2012 እኤአ)፡፡ እነዚህ ተቋማት በማቋቋሚያ አዋጃቸው የተሰጣቸውን ተልዕኮ ለማሳካት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ በይበልጥ ለሙስና የመጋለጥ ሥጋት ያለበትን አሠራር በመለየትና ቅድሚያ በመስጠት ሙስናን የመከላከል ሥራ መሥራት የበለጠ ውጤታማ የሚያደርግ ነው፡፡ በትምህርት ተቋማት ከመማር ማስተማር ጋር በተያያዘ በፈቃድ አሰጣጥ፣ ሀሰተኛ መረጃ በመስጠት፣ የማስፋፊያ ግንባታ፣ በግዥ፣ በጀት አጠቃቀምና መሰል ተግባራት ለሙስና ሊጋለጡ ይችላሉ" (አይ.ኤም.ኤፍ፣2000 እኤአ)፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት በትምህርት ሴክተሩ ሥር በተዘረዘሩ ተቋማት ውስጥ በይበልጥ ለሙስና ሊጋለጥ የሚችልን አሠራር በመለየትና የተጋላጭነት ደረጃ በመስጠት እና የሙስና ወንጀል እንዳይፈጸም የአሠራር ክፍተትን መቅረፍ የሚያስችል የመፍትሄ ሃሳብ በሚያመላክት መልኩ ከመካሄዱም በላይ ጥናቱ የተካሄድባቸው ተቋማት ያለባቸዉን ክፍተት እንዴት መሙላት እንዳለባቸዉና ከሙስና ስጋት ነፃ እንዴት ሊሆኑ እንደሚችሉ እና በትምህርት ዘርፉ ሙስና ቢከሰት ምን ጉዳት ያመጣል በሚለው ጠቃሚ ምክረ ሃሳቦችን ባካተተ መልኩ ተከናውኗል፡፡

1.2. የጥናቱ መነሻ ችግሮች (Statement of the Problem)

በትምህርት ሴክተሩ ስር የሚገኙ ተቋማት ለሙስናና ብልሹ አሠራር ተጋላጭ እንዲሆኑ ከሚያደርጉ ምክንያቶች መካከል የላላ የቁጥጥር ስርአት፣ የመመሪያዎች ግልጽነት ማነስ፣ የሚመደቡ ከፍተኛ በጀቶችና ድጎማዎች መኖራቸው፣ ሙያዊ ስነምግባር አለማክበር፣ ውስን የሆነ የአገልግሎት ተደራሽነት፣ አነስተኛ ክፍያ፣ የመረጃ አያያዝ ችግር፣ ከፍተኛ የሆነ ግዥ እንዲሁም በሥራዎች ላይ የተዋናዮች መብዛት ከዋና ዋናዎቹ ችግሮች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ የትምህርት ሴክተሩ የሙስና ስጋት ያጠላበት ቢሆንም ከዚህ በፊት የሙስና መንስኤዎችንና ያለበትን ደረጃ፣ የስጋቱ መከሰት እድልና ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ሊያሳይ የሚችል ሰፊ የሙስና ስጋት ጥናት በሴክተር ደረጃ ስለመከናወኑ መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ከሌሎች በሴክተሩ ከተጠኑ ጥናቶች በተለየ መልኩ በትምህርት ሴክተር ሥር ከሚገኙ ተቋማት መካከል በይበልጥ ለሙስና ሥጋት የተጋለጠን አሠራር በጥናት ለመፈተሽ፣ ደረጃ ለመስጠት፣ የመፍትሄ ሃሳብ ለማስቀመጥና ለወደፊት ለሌላ ጥናት መነሻ ሊሆኑ የሚችሉ ሃሳቦችን ለማመንጨት ታስቦ የተካሄደ ጥናት ነው፡፡

1.3. የጥናቱ ዓላማ (Objective of the Study)

አጠቃላይ ዓላማ፡ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማው በትምህርት ሴክተሩ ስር በሚገኙ ተቋማት የሙስና ሥጋት ጥናት ማካሄድ ሲሆን የሚከተሉት ንዑስ አላማዎችን አካቷል፡፡

ንዑስ አላማዎች፡ በትምህርት ሴክተሩ ሥር በሚገኙ ተቋማት አሠራር ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስና ስጋቶችን መለየት፣ የሙስና ስጋቶችን መተንተን እና የሙስና ስጋት ምዘና ማድረግና በተሰጠው የደረጃ ቅደም ተከተል መሠረት ሙስናና ብልሹ አሠራርን መከላከል የሚያስችል ምክረ ሃሳቦችን ማስቀመጥ ናቸው፡ ፡

1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት (Significance of the Study)

ይህንን ጥናት ስፖንሰር ያደረገው የፌዴራል የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እስከሆነ ድረስ ኮሚሽኑ በራሱ መንገድ ለፖሊሲ ግብአት ሊጠቀምበት ይችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከዚህ በኋላ ከሙስና ጋር በተያያዘ ለሚደረጉ ጥናቶች እንደ አንድ ማጣቀሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

1.5. የጥናቱ ውስንነት (Limitation of the study)

ጥናቱ የተካሄደው በትምህርት ሴክተር ላይ ቢሆንም ሁሉንም የትምህርት ተቋማት ማዳረስ ስላልተቻለ በሴክተሩ ውስጥ ያለውን የሙስና ስጋት ሙሉ በሙሉ ማሳየት አለመቻሉ የመጀመሪያው ስጋት ነው፡፡ በመረጃ መሰብሰብ ወቅት የነበረው የቋንቋ አለመግባባት ችግርም በተሰበሰበው መረጃ ላይ የራሱ ተፅእኖ አልነበረውም ማለት አይቻልም፡፡

ክፍል 2፡ የጥናቱ ስነ ዘዴ

2.1. የጥናቱ ቦታ (Study Area)

ይህ ጥናት የተካሄደው በፌደራል ደረጃ በትምህርት ሚኒስቴር፣ በመንግስትና በግል ዩኒቨርሲቲዎች፣ በፈተናዎች እና ምዘና አገልግሎት፣ በትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን ሆኖ በሁለት ክልሎች በኦሮሚያና በደቡብ እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ በተመረጡ የትምህርት ተቋማት ላይ ነው፡፡ በአጠቃላይ ጥናቱ የተካሄደባቸው ቦታዎች፤ በአዲስ አበባ በ3 ክፍለ ከተማዎች፣ በአራዳ፣ በቦሌ እና በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማዎች፣ በኦሮሚያ በሶስት ዞኖች ፤ በጅማ፣ በምስራቅ ሸዋ እና በምዕራብ አርሲ እና በደቡብ ክልል በጋሞ፣ በጉራጌና በወላይታ ዞኖች ነው፡፡

2.2. የጥናቱ ንድፈ-ሃሳብ (Research design)

ሙስናና ብልሹ አሠራር በትምህርት ሴክተሩ የሚያደርሰውን የሙስና ሥጋት ጥናት ለማካሄድ ዓይነታዊ እና የአሃዛዊ(mixed approach) የጥናት ዘዴዎችን በመጠቀም ጥናቱ ከየካቲት 9 እስከ ሚያዝያ 20 ቀን 2014 ዓ.ም ተካሂዷል፡

2.3. የጥናቱ ተሳታፊዎች (Study Participants)

ይህ ጥናት በዋነኝነት በትምህርት ሴክተሩ ስር በሚገኙ 61 ተቋማት ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ በዚህ ጥናት የተሳተፉት ከትምህርት ሚኒስትር፤ ከትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት፣ ትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን ፤ ከምዘናና ብቃት ማረጋገጫ፣ ከመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች፣ ከግል ዩኒቨርሲቲዎች፣ ከመንግስት ኮሌጆች ፣ ከግል ከሌጆች ፤ከቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች፤ ከክልል ትምህርት ቢሮዎች ፣ከቴክኒክና ሙያ ቢሮዎች ፤ ከዞን ትምህርት መምሪያዎች፣ ከዞን ቴክኒክና ሙያ መምሪያዎች፤ ከመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ ከግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፤ ከመንግስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ፣ ከግል አንደኛ

ደረጃ ትምህርት ቤቶች፤ 973 መጠይቅና 92 ቃለ መጠይቅ በድምሩ 1065 ተሳታፊዎችን በማካተት የተካሄደ ጥናት ነው፡፡ ስለሆነም ዝርዝር የናሙና መጠንን የያዘ መረጃ አባሪ ሀን ይመልከቱ፡፡

2.4. የናሙና አመራረጥ ስልት (sampling techniques)

የዚህ ጥናት ናሙና አወሳሰድ ዘዴ ከወሳኝ የናሙና አመራረጥ ዘዴዎች መካከል የሆነውን ዓላማ ተኮር ዘዴን (purposive sampling method) በመከተል የጥናቱ ተሳታፊዎችን የለየ ሲሆን በተቋማት ውስጥ ባሉ አሠራሮችና የስራ ሂደቶች ውስጥ ለሙስና ሥጋት የሚሆኑ የአሠራር ክፍተቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት የተከሄደ ጥናት ነው፡፡

2.4. መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች (Data collection methods)

ደረጃ 1፡ የዝግጅት ምዕራፍ (ተሳታፊዎችን መለየት)

የተሳካ የፀረ-ሙስና ስጋት ጥናት ለማድረግ ለሙስና ስጋቶች የተጋለጡትን የተቋሙን ስራዎች እውቀት ካላቸው ሰራተኞች ተሳትፎ ግብአት ተወስዷል፡፡ በተቋሙ ስር በሚገኙ ለሙስና ተጋላጭ ይሆናሉ ተብለው በሚታሰቡ የስራ ክፍሎች ባሉ ተግባራት ላይ የሚገኙ ሰራተኞች ተካተዋል፡፡ እንዲሁም በተቋሙ ውስጥ በተለያየ ደረጃ ያሉ ግለሰቦች (ከከፍተኛ አመራር እስከ ዝቅተኛ ሰራተኞች) የተሳተፉ ሲሆን የጥናት ቡድኑ ለጥናቱ መረጃ መሰብሰብ ከመጀመሩ በፊት ጥናቱ የሚካሄድበትን ተቋም ሰራተኞች የሙስና ስጋት ጥናት አንድምታውን፣ አላማውን እና አስፈላጊነቱን በሚገባ በማስተዋወቅ ተጀምሯል፡፡ ጥናቱ ሙሰኞችን የሚፈልግ ሳይሆን ውጤታማ የመከላከያ መሳሪያ ለመንደፍ የተካሄደ ጥናት ከመሆኑም በተጨማሪ ተቋሙን በመልካም ታማኝነት፣ በመልካም ስምና የዜጎች እምነት እንዲጨምር የሚረዳ መሆኑን ለተሳታፊ ሰራተኞች ገለፃ ተደርጎላቸዋል:: ማለትም ይህ ጥናት የተቋሙን የሙስና ስጋት ለመቀነስ ታስቦ የተሰራ እንጂ ምርመራ እንዳልሆነ ለተቋሙ ሰራተኞች አፅንዖት ተሰጥቷል፡፡ ይህ ገለፃ ትክክለኛ፣ ታማኝነት ያለዉ እና የተሟላ ፍሰት ያለዉ መረጃ ከመሰብሰብ አኳያ የራሱ የሆነ አወንታዊ ተፅኖ አለው:: የጥናት ቡድኑ የሙስና ስጋቶችን እምነት ለመገንባት የአእምሮ ማጎልበት (trust building brainstorming)፣ መጠይቅ (questionnaires/ indicators)፣ ቃለ መጠይቅ (in-depth interviews)፣ የሰነድ ትንተና (document reviews) እና የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሟል:: በሌላ በኩል የጥናት ቡድኑ የአንድ ተቋም አስተዳደር፣ ተቋማዊ መዋቅር፣ ሚናዎች እና ኃላፊነቶች እንዲሁም የግዥ ሂደቶችን እና የሰራተኞች አስተዳደርን የመሳሰሉ በተወሰኑ ሂደቶች ዙሪያ ያለውን አውድ ገምግሟል:: ሊታሰብባቸው የሚገቡ ዋና ዋና ጉዳዮችን ማለትም የመንግስት ሰራተኞች ቅጥር፣ እድገት እና ስነምግባር የሚቆጣጠሩ ህጎች፣ መመሪያዎች እንዲሁም የጥቅም ግጭትን የሚሸፍኑ የታማኝነት እና የፀረ-ሙስና ህጎች በየተቋማቱ መኖራቸውን እና በስራ ላይ መሆናቸውንም የማረጋገጥ ስራም ሰርቷል::

ደረጃ 2፡ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስና ስጋቶችን መለየት

የዚህ ደረጃ አላማ የተቋሙን ውስጣዊ እና ውጫዊ ሁኔታን ለመተንተንና ሙስና ሊከሰት የሚችልበትን ዳራ (የት፣ መቼ፣ ለምን እና እንዴት ሊከሰት ይችላል የሚለውን) እና የስጋት ሁኔታ መለየት ነው፡፡ የዚህ አላማ ተቋሙ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ጉዳት ሊደርስበት የሚችልባቸውን ሁሉንም አይነት የሙስና ስጋቶች መዘርዘር ሳይሆን ይልቁንም ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮችን ሊወስኑ የሚችሉበት ተጨባጭ እና ሊታከም

የሚችል የስጋት ዝርዝር ማውጣት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ በአንድ የተወሰነ ተቋም ውስጥ በተለመደው አሠራር ውስጥ የሚከሰቱ ተጨባጭ የሙስና ስጋት ዓይነቶች ላይ ብቻ ማተኮር ይሆናል፡፡ ይህ ደረጃ በጥንቃቄ የተመረጡ የተቋሙን ሰራተኞች ያካተተ እና ስለ ተቋሙ የቅርብ ጊዜ የሙስና ልምዶች እውቀት ያላቸው በመሆኑ መዝገቦችን ለማግኘት እና ለመገምገም የሚያስፈልገውን ጊዜ ለመቀነስ ይረዳል፡፡

ሀ. ከተቋሙ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን መሰብሰብ እና መተንተን (ውጫዊ እና ውስጣዊ እይታ)

በመጀመሪያ የጥናት ቡድኑ ድክመቶችን እና የሙስና ስጋቶችን ለመለየት የሚረዱትን ሁሉንም የመረጃ ምንጮችን ገምግሟል፡፡ የጥናት ቡድኑ ከተጠቀመባቸው መረጃዎች መካከል የውስጥ ቁጥጥር እና ኦዲት ሪፖርቶች፣ የዜጎች ቅሬታዎች፣ የጠቋሚዎች መረጃ፣ የሙስና ጉዳዮች፣ የሁኔታዎች ትንተና (የመገናኛ ብዙሃን ዘገባዎች፣ የህዝብ አስተያየቶች፣ የዳሰሳ ጥናቶች፣ የሥራ አካባቢ ውስጣዊ ቅኝቶች፣ ከሠራተኞች ጋር የተደረጉ ቃለመጠይቆች እና የመሳሰሉት)፣ የፖሊሲ እና የህግ ማዕቀፎች፣ የውስጥ ደንቦችን፣ መመሪያዎች እና የአሰራር ሂደቶች (ግልጽ ያልሆኑ ደንቦች፣ ግልጽነት ማጣት፣ የመተዳደሪያ ደንቦች አለመመጣጠን፣ ለተመሳሳይ ጉዳይ በጣም ብዙ ደንቦች መኖር እና የቁጥጥር እጥረት) ናቸው፡፡

ለ. ሁሉንም ተዛማጅ ስጋቶች ለመለየት ቦታዎችን፣ ሂደቶችን፣ ተግባራትንና አመላካቾችን መለየት

በመቀጠል የጥናት ቡድኑ የሚከተሉትን ለይቷል፤ (1) የተቋሙን ዋና ቦታዎች፣ (2) ሁሉንም ሂደቶች እና ተግባራት ለእያንዳንዱ አካባቢ እና (3) የስጋት መንስኤዎች ወይም አመላካቾች፡፡

ሐ. ለሙስና መከሰት የሙስና ስጋቶችን መለየት

ሁሉም አካባቢዎች እና ሂደቶቻቸው ከተለዩ በኋላ፤ የጥናት ቡድኑ በእያንዳንዱ ሂደት ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ስጋቶች ለመለየት ጥረት አድርጓል፡፡ ለእንደዚህ ዓይነት ጥናት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሶስቱ አማራጮች ወይም መንገዶች በጣም የተለመዱ ናቸው፡፡ ስለ ስጋቶች የቡድን አባላትን እና የተቋሙ ሰራተኞችን በሃሳብ ማጎልበት (brainstorm) እና ሁሉንም አስፈላጊ መረጃዎችን፣ ህጎችን ፣ ጠቃሚ የሆኑ የመረጃ ቋት፣ የሚዲያ ዘገባዎችን፣ የኦዲት እና የቁጥጥር ዘገባዎችን መጠቀም፡፡ ይሁን እንጂ ለሂደቶች ግምገማ ሁሉንም አመልካቾች መለየት ፈጽሞ የማይቻል ነው፡፡ ስለሆነም ሃሳቡ በመጀመሪያ ደረጃ ሁሉንም አስፈላጊ መረጃዎች (የውስጥ፣ የውጭ ቁጥጥር እና የኦዲት ዘገባዎች፣ ደንቦች፣ የህግ ማዕቀፎች፣ የውስጥ ደንቦች እና አካሄዶች፣ የዜጎች ቅሬታዎች፣ የሙስና ጉዳዮች፣ የመገናኛ ብዙሃን ዘገባዎች፣ ቃለመጠይቆች) ትክክለኛና ጥራት ያለው ጥልቅ ትንተና እንዲሰጥ ታስቦ የተደረገ ጥረት ነው፡፡ ሁሉንም የሙስና ስጋቶችን ለመፈተሽ ዓላማ በማድረግ ሰራተኞችን እና ሌሎች የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም ቦታዎች እና የስራ ሂደቶች ተለይተዋል፡፡ በመቀጠልም ሂደቶቹ በሙስና ስጋት ጠቋሚዎች አማካኝነት ተገምግመዋል፡፡

ደረጃ 3፡ የሙስና ስጋቶችን መተንተን

የጥናት ቡድኑ ሊያስከትሉ የሚችሉ ስጋቶችን ዝርዝር ካወቀ በኋላ፣ የእነዚያን ስጋቶች ምንነት እና የስጋቱን መንስኤዎች ለማወቅ የመረጃ ትንተና አካሂዷል፡፡ በዚህ ደረጃ የተከናወኑ ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡-

የተቋሙን ሰራተኞች ቃለ መጠይቅ ማደረግ፡- ከተቋሙ ሰራተኞች (የሂሳብ ባለሙያዎች፣ የግዥ ኦፊሰሮች፣ የውስጥ ኦዲተሮች ወይም ሌሎች በተለይ የተቋሙ በሙስና ስጋት ዙሪያ በቂ መረጃ አላቸው ከሚባሉ ሰዎች) ጋር የተደረጉ ቃለ-መጠይቆች እንዲሁም በሃሳብ ማጎልበት የተገኙ ግኝቶችን በመተንተን የሙስና

ስጋት አይነቶችን፣የመከሰት ዕድላቸዉንና ቢከሰቱ ሊያስከትሉ የሚችሉትን ተፅኖ የመተንተን ስራ ተከናዉኗል፡፡

የውስጥ ሰነዶችን መመርመር፡- የውስጥ ሰነዶች (ቅሬታዎች፣ የዲሲፕሊን ሂደቶች እና ያለፉ ጉዳዮች፣ የኦዲት ሪፖርቶች/ግኝቶች፣ ያለፉ የምርመራ ውጤቶች) ድክመቶችን ለመለየት እና አስቀድሞ ተለይተው የታወቁትን ስጋቶች የበለጠ ለመተንተን ይረዳሉ። በሙስና ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ ያልተለመዱ ሁኔታዎችን ለመለየት የግዥ እና የሂሳብ መዛግብት እና ሌሎች ተዛማጅ መዛግብት የመገምገም ስራ ተከናዉኗል። ተመሳሳይ ጥናቶች እንደሚሉት እንደዚህ አይነት መረጃ በቀላሉ የማይገኝ ከሆነ፣ የሙስና ቅነሳ እቅዱ ለወደፊት መገኘቱን ለማረጋገጥ ድንጋጌዎችን ማካተት የግድ ይላል፡፡

የወቅቱ የሙስና ቁጥጥር ግምገማ፡- ይህ አሁን ያሉትን መቆጣጠሪያዎች እና ሂደቶች አግባብነት፡ ብቃት እና ውጤታማነት ለመገምገም ይረዳል፡፡ የተነደፉባቸውን የሙስና ዓይነቶች መከላከል እንዳልቻሉ የሚያሳይ ማስረጃ አለ? አስተዳደሩ በተደጋጋሚ ያሉትን የሙስና ቁጥጥሮች ይሽራል? (ለምሳሌ፣ በክፍያ ትዕዛዞች ላይ የሁለተኛ ፊርማ አስፈላጊነት ብዙ ጊዜ ይሰረዛል?) እንደነዚህ ያሉት ማፈንገጦች አሁን ባለው የሙስና ቁጥጥር ውጤታማነት ላይ መበላሸትን የሚያሳይ ማስረጃ ሲሆን እነዚህ ቁጥጥሮች እንደገና መፈተሽ እንዳለባቸው የሚያሳይ ጠንካራ ምልክት ነው። የዚህ ትንታኔ ውጤት ስጋት መንስኤው ከሚከተሉት አንዱን መሆኑን ለመወሰን ነው፡- (1) ቁጥጥር (ሂደቶች ተገቢ እና በቂ ናቸው)፡ (2) ከፊል ቁጥጥር (መለኪያውን ማዘመን እና ማሟያ ያስፈልጋል) እና (3) ቁጥጥር ያልተደረገበት (ሂደቶች የሉም ወይም በቂ አይደሉም)፡፡ ስጋትን በዚህ መንገድ መመደብ በተለይ ስለ ተጽእኖው በሚያስቡበት ጊዜ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

2.5. የመረጃ ትንተና ዘዴ (Methods of Data Analysis)

የጥናት ቡድኑ የሙስና ስጋት ጥናት ለመተንተን የገላጭ እና የግምታዊ የትንተና ዘዴዎችን ስራ ላይ አዉሏል፡፡ በመሆኑም ከገላጭ የትንተና ዘዴዎች መካከል ሰንጠረዥ፣ ጥምርታ፣ ገላጭ ስዕል፣ ፐርሰንት እና ሌሎችን በዋናነት የተጠቀመ ሲሆን ወደፊት እንዳስፈላጊነቱ ግምታዊ የመረጃ ትንተና ዘዴ የሚጠቀም ይሆናል፡፡

ደረጃ 4፡ የሙስና ስጋቶችን መገምገም/መመዘን

አንድ ተቋም ሊያጋጥመው የሚችለውን እያንዳንዱን የሙስና ስጋት መለየትና መፍታት ተግባራዊ ሊሆን የማይችል እና አስቸጋሪ የመሆን ዕድሉ ከፍተኛ ነው። ስለሆነም የጥናት ቡድኑ በቅንጅት እቅድ (ለእያንዳንዱ ተቋም) ውስጥ የትኞቹ የሙስና ስጋቶች ቅድሚያ እንደሚሰጡ ገምግሞ መለየት አለበት። በተጨማሪም ተጨባጭ እና ሊመራ የሚችል የሙስና ተጋላጭነቶች ዝርዝር ከተዘጋጀ በኋላ ለእያንዳንዱ የሙስና ስጋት ሁለት የተለያዩ ግምቶችን ታሳቢ አድርጎ መረጃ ሰብስቧል፡፡ እነሱም የስጋቱ የመከሰት እድል እና ስጋቱ ከተከሰተ ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት ናቸው። ከእነዚህ ተለዋዋጮች መካከል የትኛውንም ለማስላት ምንም አይነት ተጨባጭ ዘዴ የለም፡፡ ነገር ግን በመረጃ የተደገፉ የተቋሙን ሰራተኞች እና የጥናት ቡድን አባላት በእውቀታቸው እና ባላቸው መረጃ በመመርኮዝ ግላዊ ግምቶችን ያስቀምጣሉ፡፡ በሙስና ስጋት ጥናት ዙሪያ ላይ የተገኙ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ብዙውን ጊዜ የግለሰቦች ግምት ትክክለኛ ሊሆን እንደሚችል ይገልጻል። ከቁጥር ግምቶች የተወሰነ ቁጥር ያላቸውን የጥራት ደረጃዎች (ለምሳሌ "ዝቅተኛ"፣ "መካከለኛ"

እና "ከፍተኛ") ተጠቅመናል። ለተለያዩ የሙስና ዓይነቶች ምላሾችን ቅድሚያ ለመስጠት እንደነዚህ ያሉ የደረጃ መለኪያዎች ብዙ ጊዜ በቂ ናቸው።

የመከሰት እድልን ለመገምገም የተቀመጡ ሚዛኖች

ዝቅተኛ: የአደጋው ክስተት የማይታሰብ ነው (ወይም አልፎ አልፎ)። **መካከለኛ**: ክስተቱ አንዳንድ ጊዜ መከሰት የሚችል ሲሆን ስለተከሰተው ሁኔታ የቀድሞ ማስረጃ ወይም እውቀት የስጋት መከሰት እድልን ይደግፋል። **ከፍተኛ**: ክስተቱ በአብዛኛዎቹ ሁኔታዎች ላይ እንደሚከሰት ይጠበቃል። ግልጽ እና ተደጋጋሚ ማስረጃዎች ወይም ስለተከሰተው ሁኔታ እውቀት የአደጋ መከሰት እድልን ይደግፋል።

ተጽዕኖ ለመገምገም ሚዛኖች

አነስተኛ: ስጋቱ ከተከሰተ፤ የንግድ ሥራ ሂደት እና የታቀዱ ተግባራት አይስተጓጉሉም ወይም ቀላል ተጽዕኖ ያለው ነው። ለምሳሌ ለአነስተኛ ፕሮጀክቶች እና አገልግሎቶች መዘግየት መርሐግብር፣ ዝቅተኛ ዋጋ ያላቸውን ንብረቶች ማጣት እና የማይመች የሚዲያ ትኩረት ሲሆን። **መጠነኛ**: ስጋቱ ከተከሰተ፤ እንቅስቃሴዎቹ በከፍተኛ ሁኔታ ይስተጓጎላሉ። ለምሳሌ የአንዳንድ አስፈላጊ ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች መቋረጥ፣ የንብረት መጥፋት፣ አንዳንድ የህዝብ አመኔታ ማጣት እና አሉታዊ የሚዲያ ትኩረት ናቸው። **ከባድ**: ስጋቱ ከተከሰተ፤ተግባራቶቹ በጣም የተበላሹ ናቸው።ለምሳሌ የሁሉም አስፈላጊ ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች መቋረጥ እና ዋና ዋና ንብረቶችን ማጣት ነው አባሪ ለን ይመልከቱ።

ሁለቱ ግምቶች ከተከሰቱ በድርጅቱ ላይ በጣም አደገኛ የሆኑት የትኞቹ እንደሆኑ ወደ አንድ መለኪያ ይጣመራሉ። እነሱን ለማጣመር በጣም ቀላሉ መንገድ የሶስት-በ-ሶስት የሙኑስና ስጋት ማትሪክስ በረድፎች ዝርዝር እድሎች እና ጉዳቶችን የሚያመለክቱ ናቸው። እድሉ እና ተጽእኖ ሁለቱም ከፍተኛ/ከባድ ከሆኑ ወይም አንዱ ምክንያት ከፍተኛ/ከባድ እና ሌላኛው መካከለኛ/መጠነኛ ከሆነ፤ ስጋቱ እንደ ትልቅ ስጋት (በጣም ጥቁር ጥላ) ይቆጠራል። ሁለቱም እድሎች እና ተፅእኖዎች ዝቅተኛ/አነስተኛ ወይም አንዱ ዝቅተኛ/አነስተኛ እና ሌላኛው መካከለኛ/መካከለኛ ከሆነ፤ ስጋቱ እንደ ጥቃቅን (ምንም ጥላ የለውም) እንደሆነ ይቆጠራል። በሁለቱ መካከል የሚወድቁት መካከለኛ (የብርሃን ጥላ) ደረጃ ተሰጥቷቸዋል። ስለሆነም የጥናት ቡድኑ በሙስና ቅነሳ ዕቅዱ ውስጥ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡትን ስጋቶች እንዲለዩ ይረዳል።

ደረጃ 5: የሙስና ስጋቶችን ለማከም ምክረ ሃሳብ ማቅረብ

ይህ እቅድ በቀደመው ሂደት ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስና ስጋቶችን ለመከላከል ተቋሙ ሊተገብራቸው የሚገቡ ቁጥጥሮችን ይገልፃል። ቁጥጥሮች ተገቢ ያልሆኑ ድርጊቶችን ለመከላከል፣ ለመፈተሽ ወይም ለመለየት፣ የተነደፉ ፖሊሲዎች፣ ሂደቶች እና የአስተዳደር ስርዓቶችን ይለያል። በመሆኑም የተቋሙ የሙስና ስጋት እንዲቀንስ ይረዳል። በመቀጠልም ዕቅዱ በዝርዝር እና በግልጽ ይቀመጣል። በስተመጨረሻ ከተወሰኑ የጊዜ ሰሌዳዎች ጋር እና በተቋሙ የአሠራር እና ስልታዊ የስራ እቅዶች ውስጥ እንዲካተት ይደረጋል።

ክፍል 3፡ የሙስና ስጋት ትንተና

በዚህ ክፍል ውስጥ በትምህርት ሴክተር ውስጥ እየታዩ ያሉ የሙስና ስጋቶች ትንተና ሪፖርት ይቀርብበታል፡፡ የሙስና ስጋት ትንተናው በሶስት ክፍሎች የተዋቀረ ሲሆን የመጀመሪያው በትምህርት ሴክተር ውስጥ እየታዩ ያሉ ስጋቶችን የሚያሳይ ነው፡፡ በትምህርት ሴክተር ውስጥ የሚታዩ ስጋቶች ከሁለት አንፃር ተብራርተው የቀረቡ ሲሆን በአስተዳደርና ፋይናንስ ውስጥ የሚታዩ ስጋቶችና በትምህርት ስራው ላይ በቀጥታ የሚታዩ ስጋቶች ተጠቃለው ቀርበውበታል፡፡ ሁለተኛው የጥናት ሪፖርቱ ክፍል ለእነዚህ ስጋቶች መነሻ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የተለዩ ምክንያቶች የቀረቡበት ነው፡፡ በመጨረሻም በትምህርት ሴክተር ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ተቋማት ሙስናን ለመከላከልም ሆነ ቢከሰት የእርምት እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል አሰራር ከመዘርጋት አንፃር ያሉበት ሁኔታ ቀርቧል፡፡

3.1. በትምህርት ዘርፍ ላይ የሚታዩ የሙስና ስጋቶች

በዚህ ጥናት ውስጥ የትምህርት ሴክተር በርካታ ተቋማትን ያቀፈ ሲሆን በነዚህ ተቋማት የሚገኙ የአስተዳደርና ፋይናንስ መረጃዎችን በምናይበት ጊዜ ተቋማቱ በጣም የተለያዩ መሆናቸውን አስቀድሞ ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ ትልቁ ልዩነት የግልና የመንግስት ተቋማት የሚለው ቢሆንም የመንግስት ሆነውም የተለያዩ አይነት ተቋማት እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡ የውስጥ ገቢ ከማመንጨት አኳያ እንደ ትምህርት ሚኒስቴር አይነት ተቋማት ምንም የውስጥ ገቢ የሌላቸው በሚል ሊታዩ ሲችሉ ከበጀታቸው ከግማሽ በላይ የሆነውን ወጭያቸውን ከውስጥ ገቢ መሸፈን የሚችሉ የትምህርት ተቋማት እንዳሉም ማየት ተችሏል፡፡ የውስጥ የቁጥጥር ስርአት ከመዘርጋት አንፃር ጠንካራ የውስጥ ኦዲት ያላቸው የትምህርት ተቋማት ሲገኙ እነዚህም በተለይም የፌዴራልና የክልል ትምህርት አስተዳደር ተቋማት ናቸው፡፡ ወደ ትምህርት ኮሌጆችና አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ስንዞር የውስጥ ኦዲት የሌላቸው በርካታ ተቋማት ይገኛሉ፡፡ እነዚህ የውስጥ ኦዲት የሌላቸው ተቋማት በክልል ኦዲተሮች በተለያዩ ወቅቶች የሚገመገሙ መሆኑን ግን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡

በተቋማቱ መካከል ያለው ልዩነት ሰፊ ቢሆንም ሁሉም በሚባል ደረጃ በውስጣቸው አስተዳደርና የፋይናንስ ክፍል አላቸው፡፡ በነዚህ ክፍሎች የሚገኙ ዋና ስራዎችም የሰው ሃብት ልማት አስተዳደር፣ የፋይናንስና በጀት፣ ግዥና የንብረት አስተዳደር ናቸው፡፡ እነዚህን የስራ ክፍሎች በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች በጣም ሰፊና የተለያዩ ናቸው፡፡ ሆኖም የጥናቱ አላማ በዘርፉ የሚገኙ የሙስና ስጋቶችን መለየት ስለሆነ ከሁሉም ተቋማት የተሰበሰቡ ስጋቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡- የሚገዙ እቃዎች የጥራት ችግር፣ የጥገና አገልግሎት ግዥ ክፍል ለብልሹ አሰራር ተጋላጭ መሆኑ፣ የበጀት ድጎማዎችን ከመደበኛው ስራ ይልቅ ላልተፈለገ እና ከዋናው ተልዕኮ ውጭ ለሆኑ የፖለቲካ ፓርቲ ስራዎች ላይ ማዋል፣ በኮሌጆችና ትምህርትቤቶች የሚከናወነው የውጭ ኦዲት ሪፖርት ለትምህርት ቢሮው ብቻ ስለሚቀርብ ሰራተኛው ክፍተቱን ወይም ግኝቱን የማወቅ እድል የሌለው መሆኑ፣ በተለያየ መልኩ የሚመጡ የድጋፍ በጀቶች አፈፃፀማቸው የተለያየ መሆኑ፡፡ ለምሳሌ፣ የስኩል ግራንት እና የብሎክ ግራንት የተለያየ አፈፃፀም ስላላቸው የበጀት አስተዳደሩ የተወሳሰበ እንዲሆን እያደረገው መሆኑ፣ ከውስጥ ገቢ የሚገኝ ገንዘብ ለብክነት የተጋለጠ

መሆኑ፣ አላስፈላጊ ግዥዎች በተለይ ከመፅሃፍ ግዥ ጋር በተያያዘ ይታያል፣ መፅሃፍ ማሳተምና ሌሎች የቢሮ እቃዎች በወረደ ጥራት መግዛት ይገኝበታል፡፡

በአስተዳደርና ፋይናንስ ክፍል በሚገኙ የተለያዩ የስራ ሂደቶች ውስጥ በእያንዳንዱ የስራ ሂደት ውስጥ የሚታዩ የሙስና ስጋቶች እንደየ ባህሪቸው እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ በቀዳሚነት በፋይናንስ ክፍል ከሚታዩ ችግሮች መካከል ዋና ዋናዎቹ ህጋዊ ያልሆነ ክፍያ መፈፀም፣ የወጪና የገቢ የሂሳብ ሰነድ ባግባቡ አለመያዝ፣ በሌለ ሰራተኛ ደሞዝ መክፈል፣ ስራ ላይ ላልዋሉ ሰዎችና በስራ ላይ ላልዋለ ቀን የውሎ አበል መክፈል፣ አንዳንድ ክፍያዎችን በወቅቱ አለመክፈል ወይም ገንዘብ በወቅቱ አለመሰብሰብ፣ ለተቋማት የተለያዩ ግብአቶችን የሚያቀርቡ ድርጅቶች ለሚያቀርቡት የዋጋ ጭማሪ ጥናት ሳያደርጉ በተጠየቀው መሰረት መክፈል፣ ለበርካታ አመታት ያልተወራረደ ሂሳብ መኖር፣ ከሚመለከተው የመንግስት አካል ፈቃድ ውጭ የባንክ አካውንት መክፈት፣ እና የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ በየእለቱ አለማድረግ ይገኙበታል፡፡ የGEQUIP(General Education Quality Improvement Program For Equity) በጀት ድጋፍ ከፍተኛ ቢሆንም ለታለመለት አላማ ሲውል ግን አይታይም የሚል ግምገማ ከመሰንዘሩም በላይ ይህ ብር ርእሰ መምህሩ እንዳአስፈለገው የሚያደርገው እንደሆነ ተገልጧል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ የግዥ ክፍል ላይ ከሚታዩ ችግሮች መካከል የሆቴል አገልግሎት ግዥ በተለይ አዲስ አበባ በሚገኙ የትምህርት ተቋማት ላይ ተደጋጋሚ የአሰራር ክፍተት ይታያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ ተቋማት ፍላጎት ያልቀረበበት የንብረት ግዥ መፈጸም፣ በመንግስት ግዥ ኤጀንሲ ከታገደ ድርጅት እቃ መግዛትና በውድድር ወይም በጨረታ ያሸነፈ ድርጅት ግልፅ ባልሆነ ምክንያት እንዲወድቅ በማድረግ ከሌላ ድርጅት ንብረት መግዛት ይገኝበታል፡፡

ከንብረት አስተዳደር ጋር በተያያዘ የሚታዩ ችግሮች ህንፃዎችንና የተገዙ ንብረቶችን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ አንዳንድ የትምህርት ተቋማት ከፍተኛ ግንባታ የሚደረግ ሲሆን ተገንብተው ያለቁ ህንፃዎችን ርክክብ አለማድረግና ርክክብ የተደረገላቸውን ህንፃዎች ደግሞ በሰነድ አለመመዝገብና የባለቤትነት ሰነድ አለመያዝ ይታያል፡፡ ተገዝተው ከሚገቡ ንብረቶች መካከል በቆይታ ንብረት ጉድለት መከሰት፣ ንብረቶች ተከማችተው ለረጅም ጊዜ እንዲቆዩ ማድረግ፣ ንብረቶችን ባግባቡ በሰነድ አለመመዝገብና አልፎ አልፎ የንበረት ጉድለት መከሰትና ለስራ መዋል ያለባቸውን ንብረቶች ባግባቡ ጥቅም ላይ አለማዋል ይታያል፡፡

ከአስተዳደር ክፍሎች መካከል አንዱ በሆነው የሰው ሃብት ልማት አስተዳደርም የሚታይ ችግር አለ፡፡ በተደጋጋሚ በተለያዩ ተቋማት የሚታየው ችግር የመምህራንና አስተዳደር ሰራተኞች በስራ ሰአት አለመገኘት ሲሆን የትምህርት ሰአት ማባከንን ያካትታል፡፡ በትምህርት ቤቶች አካባቢ የታየው ሌላ ችግር ከደረጃ እድገት ጋር በተያያዘ ግልፅነት የጎደለው አሰራር መጠቀሱ ነው፡፡ ከእነዚህ በተጨማሪ ደንበኛን ባግባቡ አለማስተናገድ፣ አስተማሪዎችና አሰልጣኞች የራሰቸውን ችሎታና አቅም በየጊዜው የማሳደግ ውስንነት መኖር፣ ዝቅተኛ የስራ ተነሳሽነት መኖርና በተወሰኑ ቦታዎች ላይ ለቅጥርና ደረጃ እድገት ሃሰተኛ የትምህት ማስረጃ ማስያዝ ይገኝበታል፡፡

የአሃዛዊ መረጃዎች እንደሚያሳዩትም የሙስና ስጋት መኖሩን የሚያመላክቱ መረጃዎች ተገኝተዋል፡፡ እንደ ማሳያ ሊቀርብ የሚችለው በጥናቱ ከተሳተፉ ሰራተኞች መካከል 65 በመቶ የሚሆኑት በተቋማቸው ውስጥ የመልካም አስተዳደር ችግሮች አሉ ብለው የሚያስቡ ሲሆን ከዚህ የሚበልጡት (ከ 66 በመቶ በላይ የሆኑት) ተሳታፊዎች ደግሞ በተቋማቸው ውስጥ የሙስና ችግር አለ ብለው ያስባሉ፡፡ በተቋማቸው ውስጥ ሙስና የለም ብለው ከሚያስቡ ተሳታፊዎች መካከል ወደ 67 ከመቶ የሚሆኑት በተቋማቸው ውስጥ ለሙስና ተጋላጭ ሊሆኑ የሚችሉ የስራ ሂደቶች እንዳሉ አመላክተዋል፡፡ ይህ የሚያመለክተው ሙስና በአንድ ተቋም ውስጥ በአሁኑ ጊዜ አለመከሰቱ ወደፊት ላለመከሰቱ ዋስትና ሊሆን እንደማይችል ነው (አባሪ ሰንጠረዥ መ6ን ይመልከቱ)፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በክፍል 4 በሰንጠረዥ ሠ1 በዝርዝር እንደሚታየው በተለያየ ደረጃ በሚገኙ ትምህርት ተቋማት ውስጥ 19 አይነት የሙስና ስጋቶች ሊከሰቱ እንደሚችሉ ለማየት ተችሏል፡፡

በተለያዩ የትምህርት ተቋማት ውስጥ የተሰበሰበው መረጃ እንደሚያሳው ከሆነ ከመማር ማስተማርና ስልጠና እንዲሁም ትምህርት አስተዳደር ጋር የተገናኙ የሙስና ስጋቶች እንዳሉም ለማየት ተችሏል፡፡ ከመምህራን ወይም አሰልጣኞች ጋር በተያያዘ ከሚነሱ ስጋቶች መካከል በመምህራን ልማት የዘመድና የፓርቲ አሰራር፣ አድልኦና ጉቦ መቀበል እንደሚከሰት ተገልጧል፡፡ በመምህራን እና ሰራተኛ አስተዳደር ክፍል ህገወጥ ቅጥር እና ዝውውር ስራና ከመምህራን አንፃር ሲታይ ደግሞ ለሁሉም እኩል ከመድረስ ይልቅ አንድ አንድ ተማሪዎች ለይቶ ለመጠቀም በማሰብ አላስፈላጊ ውጤት የመስጠት አንዳንዶቹ ደግሞ ውጤት ማግኘት ሲገባቸው አለማግኘት የመሳሰሉ ችግሮች ይታያሉ፡፡ የመምህራን ቅጥር ላይ ተቀራራቢ ዉጤት ሲመጣ አንዱን በትዉዉቅ የማሳለፍ ነገር በተወሰኑ ቦታዎች ይታያል፡፡

ከሃሰተኛ የትምህርት ሰነድ ጋር በተያያዘ የብቃት ማረጋገጥ እና ፈቃድ የስራ ክፍል መስፈርት የማያሟሉ ተቋማትን ፈቃድ መስጠትና የፈቃድ እድሳት ስራ መስራት በመጀመሪያ ሊጠቀስ ይችላል፡፡ በትምህርት ቤት አካባቢ የ8ኛ ክፍል የትምህርት ማስረጃዎች ሐሰተኛ ሆነው የተገኙበት አጋጣሚ ተከስቷል፡፡ ከመምህራንና የትምህርት አስተዳደርና አመራር ላይ ያሉ ሰራተኞች ሃሰተኛ የትምህርት ማስረጃ የተገኘባቸው የትምህርት ተቋማት እንዳሉና እንደ ኦሮሚያ ባሉ ክልሎች ላይ ክትትል ተደርጎ ብዙ ሰዎች ላይ እርምት ርምጃ እንደተወሰደ ማየት ተችሏል፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ የትምህርት ማስረጃ የማጣራት ስራ ሲጀመር ሰራተኞች የመልቀቅ አዝማሚያ እንዳሳዩ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በግል ኮሌጆች ሰልጣኞች የሲ.ኦ.ሲ. ምዘና እንዲያልፉ ያልተገባ ድጋፍ ማድረግና ባግባቡ ተምረው ላልጨረሱ ሰዎችና ፈፅሞ ላልተማሩ ሰዎች የትምህርት ማስረጃ ፕሪንት አድርጎ መሸጥ እንደሚታይ የተወሰኑ መረጃዎች አመላክተዋል፡፡ ከዚህ አንፃር አንዳንድ የግል ኮሌጆች የትምህርት ማስረጃን እውነተኛነት በተመለከተ ተደጋጋሚ ጥያቄ ከመንግስት አካላት እንደሚላክላቸውና ምላሽ እንደሚሰጡ ተቁመዋል፡፡

በሬጅስትራር አካባቢ የሚታየው ችግርም የትምህርት ዘርፉ ውስጥ በቀጥታ ከመማር ማስተማር ጋር የሚገናኝ ስጋት ነው፡፡ በኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች በሚገኙ ሬጅስትራሮች ውስጥ የተማሪዎችን ውጤት የማሳሳትና ከዚያም አልፎ የማጭበርበር ተግባር ይፈፀማል፡፡ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ የሚሰጡ

የሬጂስትራር ሰራተኞች እንዳሉም መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ይህ ችግር በግል ተቋማት ብቻም ሳይሆን በመንግስት ተቋማትም ሊከሰት የሚችልበት እድል ታይቷል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ስጋቶች በተጨማሪ በተለያዩ የስራ ክፍሎች ውስጥ በትምህርት ስራው ላይ የሙስና ስጋት ይታያል፡፡ በአንዳንድ ቦታዎች ፕሮጀክት ላይ ሥራው ሳይሰራ ክፍያ ማጽደቅ፣ የስራውን ጥራት ለድርድር ማቅረብና በኔትወርክ መስራት ይከሰታል፡፡ የመምህራን እና የሰራተኛ አስተዳደር፣ የትምህርት ቤቶች ብቃት ማረጋገጥ እና ፈቃድ የሚሰጠው የስራ ክፍሎች ላይ ስጋቶች እንደሚታይ መረጃ ሰጭዎች ጠቁመዋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የተቋማት ፈቃድ እና እድሳት የሚሰጡ ተቋማት የሚሰጡት አገልግሎት በርካታ ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ጋር ስለሚገናኙ የሙስና ስጋት እንዳለባቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

3.2. ለሙስና መከሰት መነሻ ምክንያት ተደርገው የሚወሰዱ ጉዳዮች

ለሙስና መከሰት ምክንያት የሆኑ ጉዳዮችን በተመለከተ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የችግሩ መነሻ በዋናነት ከሶስት ጉዳዮች ጋር የተያያዘ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የመጀመሪያው ከግለሰቦች ስነምግባር አቋም ወይም የሞራል ልእልና ጋር የሚገናኝ ነው፡፡ በሰዎች ዘንድ የሚታዩ የስነምግባር ችግሮች ሲባል ሳይሰሩ በአጭር ጊዜ ለመክበር መፈለግ ወይም የሰዎች ገንዘብ የማግኘት ፍላጎት እጅግ ከፍተኛ መሆን፣ የሞራል መላሸቅ ወይም ሠራተኛው ዋልጌነት፣ ሱስ ለማርካት፣ ግልፅ አሰራር ያለመውደድ፣ መመርያና ደንብ ጠንቅቆ አለማወቅ፣ ገዬሌሽነት፣ የስራ ሃላፊነት የመውሰድ ዝቅተኛ ተነሳሽነት እና የማህበረሰቡ አመለካከት መቀየር የሚባሉ ምክንያቶችን ያካትታል፡፡

ሁለተኛው መንስኤ ከአሰራር ጋር የተያያዘ ነው፡፡ አሰራር ሲባል በየተቋማቱ የሚገኙ አመራሮች ያላቸው ተነሳሽነትና ያላቸው አርአያነት፣ በተቋሙ የተወሰዱ የእርምት እርምጃዎችና ሙስናን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተዘረጉ አሰራሮችን የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ አውድ ውስጥ ብዙ ምክንያቶች ከመረጃ ሰጭዎች ለመሰብሰብ ተችሏል፡- የተጠናከረ የቁጥጥር ስርአት አለመኖር፣ የአመራሩ ልል መሆን፣ የህግ መላላት፣ ለተፈጸሙ ወንጀሎች መፍትሄ ያለማግኘት፣ የፍርድ ቤት ማጉላላት፣ የሚሰራን ሰው አለማበረታታት፣ ግልፀኝነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር አለመኖር፣ ሰራኞች በብቃታቸውና ችሎታቸው ተመዝነው አለመቀጠር፣ ስልጠና አለመኖር፣ ማበረታቻ (Motivation) አለመኖር፣ እና ፍትሐዊ አስተዳደር አለመኖር ሊሆኑ እንደሚችሉ ተመላክቷል፡፡

ከኢኮኖሚ ወይም ከገቢ መጠን ጋር የሚነሱ ችግሮችም በሶስተኛነት ሊታዩ ይችላሉ፡፡ ከኢኮኖሚ አንፃር በርካታ መረጃ ሰጭዎች እንደገለጡት የሰራተኛዉ ገቢ ማነስ ወይም መንግስት ለሰራተኞች የሚከፍለዉ ደመዎዝ እና የኑሮ ደረጃዉ አለመመጣጠን እና የሰዎች ገንዘብ የማግኘት ፍላጎት እጅግ ከፍተኛ መሆኑ ለሙስና በር የሚከፍት ሁኖ ተጠቅሷል፡፡ የገቢ ማነሱ ግለሰቦች ሌሎች አማራጮችን እንዲመለከቱና ወደ ሙስና እንዲገቡ ያደርጋል የሚል ግምት ታይቷል፡፡

እነዚህን ምክንያቶች በሌላ መልኩ ለማየት እንዲረዳ በሚል በትምህርት ዘርፍ ውስጥ ያሉ ሰራተኞች ለሙያቸው ያላቸው ክብርና የሚያንፀባርቁት የሙያ ስነምግባር ምን ያህል እንደሆነ ለማየት ተሞክሯል፡፡

የተለያዩ መረጃ ሰጭዎች የተለያዩ ሃሳቦችን አንፀባርቀዋል፡፡ የተወሰኑ ሰዎች ሁሉም ሰራተኞች ለሙያቸው ታማኝ ናቸው ማለት እንደሚከብድና ሙያቸውንና ስራቸውን አክብረው የሚሰሩ እንዳሉ ሁሉ የማይሰሩም እንዳሉ ጠቅሰዋል፡፡ ሌሎች ደግሞ ከሙያ ስነ ምግባር ይልቅ ለፖለቲካ እንደሚያደሉና ከሙያ አፈጻጸም ይልቅ ከአለቃ ጋር ባላቸው የማቃጠር ስራ ብቻ ተጠቃሚ ለመሆን የሚሞክሩ አሉ፡፡ ሌሎች መረጃ ሰጭዎች ደግሞ በትምህርት ተቋማት የሚገኙ ሰራተኞች ለሚሰጣቸው ሃላፊነትና ለሙያው ስነ ምግባር ታማኝ እና ሃቀኛ እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡ እንደ ማሳያ የሚጠቅሱት ደግሞ መምህራን ሰአት እንደሚያከብሩና ስራወቻቸውን በእቅድ ይመራሉ የሚል ነው፡፡ ነገር ግን ከዚህ በፊት እንደተገለፀው ሁሉም መምህራን የሙያ ስነምግር አላቸው ብሎ ለመውሰድ አስቸጋሪ መሆኑን የሚያመላክቱ ችግሮች እንዳሉ መጠቀሱን ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡

3.3. ከሙስና ስጋት አንፃር የትምህርት ተቋማት ያሉበት ሁኔታ

የትምህርት ተቋማት ሲባሉ በቀጥታ የትምህርት አገልግሎት የሚሰጡ ትምህርት ቤቶችን፣ ኮሌጆችንና ዩኒቨርሲቲዎችን ጨምሮ በትምህርት አስተዳደር ከፌዴራል ትምህርት ሚኒስቴር ጀምሮ እስከ ወረዳ ትምህርት ፅ/ቤት ድረስ ያሉ ተቋማትን የሚመለከት ነው፡፡ በእነዚህ ተቋማት አመራሩና የተዘረጉ አሰራሮች የሙስና ችግርን በተመለከተ የራሳቸው ሚና አላቸው፡፡ በየተቋማቱ የሚገኙ አመራሮችና የተዘረጉ ስርአቶች ሙስናን በመከላከልና ከተከሰተም የእርምት እርማጃ ለመውሰድ በጥሩ ተቋማዊ ቁመና ላይ መገኘት እንዳለባቸው ይጠበቃል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ተቋማት ያሉበት ሁኔታ በሁለት መልኩ ይቀርባል፡፡

3.3.1. በትምህርት ተቋማት ያለው የአመራር ሁኔታ

ተቋማት ሙስናን ለመከላከልም ሆነ ለመቆጣጠር የሚችሉበት ሁኔታ ላይ መሆናቸውን ለማየት በቀዳሚነት ሊነሳ የሚችለው በየተቋማቱ የሚገኘው የአመራር ሁኔታ ነው፡፡ አመራርን በተመለከተ በግል የትምህርት ተቋማት የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደሚያሳዩት አብዛኞቹ ውሳኔዎች የሚወሰኑት በማዕከል እንደሆነና ለተቋማቸው መልካም ስም ቅድሚያ የሚሰጡ መሆናቸውን ለማየት ተችሏል፡፡ ወደ መንግስት ተቋማት ስንዞር ግን የተለያዩ ሃሳቦች ይንፀባረቃሉ፡፡ ከተወሰኑ ቦታዎች የተገኙ መረጃዎች የሚያሳዩት አመራሩ ሰነድ ማዘጋጀት ላይ ጥሩ ሲሆን እነዚህ ሰነዶች መተግበር ላይ ግን ችግር ይታይበታል፡፡ ለዚህም እንደምክንያትነት የሚቀርበው አመራሩን ተጠያቂ የሚያደርግ ስርዓት የለም የሚል ነው፡፡ ከዚህ በተቃራኒው ለውጥ ለማምጣት በምሳሌነት የሚሰሩ አመራሮች እንዳሉም የተናገሩ ሰዎች አሉ፡፡ እነዚህም አመራሮች ተቋማቸውን በአግባቡ የሚከታተሉ ወይም የስራ ግምገማ በማድርግ አስፈጊውን የእርምት እርምጃ የሚወስዱ ናቸው፡፡

ከአሃዛዊ መረጃዎች የተገኙ የጥናት ውጤቶች እንደሚያሳዩት ከሆነ ብዛት ያላቸው (ከሁለት ሶስተኛ በላይ) የጥናቱ ተሳታፊዎች በተቋማት የሚደረገው የስነምግባር መከታተያ ክፍልን አቅምና ብቃት ለማሳደግ የሚደረገው ጥረት አመርቂ አለመሆኑን አመላክተዋል፡፡ በተለይም ከአራቱ ተሳታፊዎች ውስጥ ሶስቱ የተቋማት የበላይ አመራሮች የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ምክረሐሳቦችን መነሻ በማድረግ ግልፅነት ያለው ተቋማዊ የአሠራር ስርዓት ለመዘርጋት የሚያደርጉት ተነሳሽነት አናሳ መሆኑን አመላክተዋል፡፡ በሌላ በኩል ተመሳሳይ አሃዝ ያላቸው ተሳታፊዎች ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በተቋማት ሙስና

እንዲቀንስና የሥነምግባር ጉድለት እንዲታረም የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋት አቅምና ብቃት እንደሚያንሳቸው አመላክተዋል፡፡ ይህ ውጤት የሚያመለክተው በተቋማት ውስጥ የተቋቋሙትን የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን አቅምና ብቃት ለማጎልበት ብዙ ስራ የሚጠብቀው መሆኑን ነው፡፡ ዝርዝር መረጃዉ በአባሪ ሰንጠረዥ መ2 ላይ ይመልከቱ፡፡

የሙሥና ሥጋትን መቀነስና በአሠራራቸዉ ገልጽነትን ማስፈን ተቋማት ሙስናን ለመዋጋት ከሚረዳቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች ውስጥ አይነተኛ ግብዓት መሆኑ አሌ የማይባል ሀቅ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ተቋማት የሙስና ተጋላጭነት ስጋትን የመቀነስ ስልታቸውንና ያላቸዉን የግልጽነት ዕድገት ደረጃን ለመለካት ጥረት አድርጓል፡፡ ተቋማት የሚከተሉትን የሙስና ስጋት መቀነሻ ስልትና ያላቸዉን የግልጽነት ዕድገት ደረጃ ዝርዝር መረጃዎች በአባሪ ሰንጠረዥ መ4 ላይ ይመልከቱ፡፡ አብዛኛዎቹ ተሳታፊ ተቋማት ባላቸው የግልጽነት ዕድገት ደረጃ ላይ አወንታዊ እይታ ቢኖራቸውም በተለይ በተቋማት ውስጥ የአመራሩና የሰራተኛዉ ብልሹ ተግባራትን የመገምገሚያ ስርዓት ከመዘርጋት አኳያ ያደረጉት ጥረት ደካማ መሆኑን የመረጃ ትንተናው ያመላክታል፡፡ በተጨማሪም ተቋማት የአመራሩንና የሰራተኛዉ የብልሹ ተግባራት መገምገሚያ ስርዓት ከመዘርጋት አኳያ ያደረጉት ጥረት በደካማነት ሊታይ የሚችል ነው፡፡ የስነምግባር ደንብም እንዲሁ ተመሳሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ እነዚህን መመሪያዎችና አሠራሮችን በመተግበር ሂደት በሚፈጠር ክፍተት የተነሳ ግን የሙስና ስጋቶች እንደሚከሰቱ ተገልጿል፡፡

3.3.2. በትምህርት ተቋማት ውስጥ ሙስናን የሚመለከቱ አሰራሮች፣ ደንቦችና መመሪያዎች

በተቋማት ውስጥ ሙስና ለመዋጋት ከሚረዱ ደንቦችና መመሪያዎች መካከል የስነ ምግባር ደንብ መኖር፣ የጥቅም ግጭት የሚያስነሱ የተለያዩ የውስጥ መመሪያዎችን ማስተካከል፣ የተጠያቂነት ስርዓት መዘርጋት፣ የቅሬታ ማስተናገጃ ስርአትና የዲሲፕሊን አሠራር መዘርጋት ይገኙበታል፡፡ በአብዛኛው የመንግስት የትምህርት ተቋማት ውስጥ እነዚህ ደንቦች ከሃገሪቱ ህግ የሚቀዱ ስለሆኑ ተመሳሳይ ሆነው ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ ሁሉም መረጃ ሰጭዎች በሚባል ደረጃ የሰው ሃይል አስተዳደርን በተመለከተ የሲቪል ሰርቪስ መመሪያ እንደሚተገብሩ ይናገራሉ፡፡

የሙስና ስጋት በቀዳሚነት የሚታየው የተቋማት አሠራር ምን ያህል ሙስና እንዳይከሰት ሊያደርግ በሚችል መልኩ የተዘረጋ መሆኑን ማሳየት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በፌዴራል ደረጃም ይሁን እስከ ወረዳ ድረስ የሚገኙ የትምህርት ተቋማትን በተለያዩ መስፈርቶች ለማየት ተሞክሯል፡፡ ከዚህ አንፃር ቀዳሚው እያንዳንዱ ተቋም የተልእኮ መግለጫ ማዘጋጀትንና ይህንንም ለሠራተኞች ማስገንዘቡን ማየት ነው፡፡ ከተሰበሰበው መረጃ እንደታየው በተግባር ላይ ከሚነሱ ውስንነቶች ውጭ የተቋሙን ተልእኮም ሆነ የእያንዳንዱን ሠራተኛ የስራ ድርሻ ለሠራተኞች የማሳወቅ ስራ እየተተገበረ ነው፡፡

ሌላኛው ከተቋማት የሚጠበቀው አሠራር በየወቅቱ የሙስና ስጋት ትንተና በማድረግ ያሉባቸውን ክፍተቶች የመለየትና የመፍትሄ እርምጃ መውሰድ ናቸው፡፡ በፌዴራል ደረጃ የሚገኙ መስሪያ ቤቶች፣ የክልል ትምህርት ቢሮዎችና በየአንዳንዱ ኮሌጆች ላይ የስጋት ትንተና እንደተደረገ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህ ትንተና

በአንዳንድ ቦታ በሰነድ ተዘጋጅቶ ለውይይት ከመቅረብ የዘለለ ስራ አልተሰራበትም፡፡ ከዚህ በተቃራኒው በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች፣ ኮሌጆች፣ ትምህርት አስተዳደር ተቋማትና ትምህርት ቤቶች ውስጥ የስጋት ትንተና ፈፅሞ እንዳልተካሄደ የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ሙስናን ከመከላከል አንፃር ከየተቋማቱ ሊጠቀስ የሚችል ጥሩ ልምድ ካለ ለማየት ጥረት ተደርጓል፡፡ አንዳንድ ተቋማት ምንም ልምድ የሌላቸው ሲሆን፣ የተወሰኑት ግን የሚያነሱት መልካም ተሞክሮ አለ፡፡ ለምሳሌ፡- የአሠራር ግምገማ በእቅድ አኳያ መፈፀም፣ የውስጥ ኦዲት ስርዓት ማጠናከር፣ በሚፈጠሩ ስህተቶች ላይ እርምጃ መውሰድ፣ ሬጅስትራር ላይ ትኩረት አድርጎ መከታተል፣ ተጋላጭ ቦታዎችን በየጊዜው መለየት፣ በሰራተኛው መካከል ስለ ሙስና ውይይት ማድረግ፣ በትምህርት ቤቶች ለተማሪዎች ግንዛቤ መፍጠር እና የሰው ሀብት ልማት አስተዳደር ግልፅ እንዲሆን ማድረግ ይገኙበታል፡፡

ከላይ የተነሱትን ጉዳዮች በአሃዛዊ መረጃ ለማሳየት እንዲረዳ በተለያዩ የትምህርት ተቋማት ሙስናን ለመከላከል የሚረዱ አሰራሮችን፣ በሚመለከተው አካል የወጡ አዋጆችን፣ መመሪያዎችንና ደንቦችን የመተግበርና ስራ ላይ መዋላቸዉን የመቆጣጠር እና ከላይ የተጠቀሱትን ስራዎች የሚያስተባብርና የሚያስፈፅም የስነምግባር መከታተያ ክፍል ማቋቋምና አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ በተመለከተ የተወሰነ መረጃ ለመሰብሰብ ተሞክሯል፡፡ ከዚህ አንፃር አብዛኛው (60%) የጥናቱ ተሳታፊዎች በመስሪያ ቤታቸው ውስጥ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 መሰረት የተቋቋመ መሆኑን ሪፖርት ያደረጉ ሲሆን ጥቂት የማይባሉ (29%) የጥናቱ ተሳታፊዎች ደግሞ በመስሪያ ቤታቸው ውስጥ የስነምግባር መከታተያ ክፍል መቋቋሙን እንደማያውቁ ገልፀዋል፡፡ ይህ ደግሞ አንዳንድ መስሪያ ቤቶች ለሰራተኞቻቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ያለመስጠታቸውን ከማሳየቱም በተጨማሪ ወደፊት በሙስና ላይ ለሚያደርጉት ትግል የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡

በሌላ በኩል ብዙሃኑ የጥናቱ ተሳታፎዎች በመስሪያ ቤታቸው ውስጥ የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ሥራዎች በተቋሙ ስትራቴጂክ ዕቅድ ዉስጥ ተካተው እንደሚተገበሩ እንዲሁም ተቋማት በሥነምግባር የታነፀ አመራር ግንባታ አሠራር ሥርዓት ነድፈው ተግባራዊ እያደረጉ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ በመሆኑም ከጥናቱ ተሳታፊዎች ውስጥ ሁለት ሶስተኛው(65%) የሚሆኑት በተቋማቸው ውስጥ የአመራርና የሰራተኞች የሥነምግባር መመሪያ እንዳለና ተግባራዊ እየሆነ እንደሆነ ገልፀዋል (አባሪ ሰንጠረዥመ1ን ይመልከቱ)፡፡ ይሁን እንጅ ቀላል የማይባሉ የጥናቱ ተሳታፊዎች(37 እና 29 በመቶ የሚሆኑት በቅደም ተከተል) በተቋማቸው ውስጥ በመልካም ሥነምግባር አርአያ የሆኑ አመራሮችንና ሠራተኞችን የመለየትና ዕውቅና የመስጠት አሠራር ሥርዓት እንደሌለና በተቋማት ውስጥ ላሉ አመራሮችና ሠራተኞች ጥራትና ተገቢነት ያለዉ የሥነምግባር አቅምና ብቃት ማጎልበቻ ሥልጠና በመደበኛ አሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ እንደማይሰጥ ገልፀዋል፡፡

ከዚህ በፊት የተካሄዱ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በተቋማት ውስጥ የመረጃ ግልፅነት መጓደልና የተቆራረጠ ፍሰት መኖር አንድን መስሪያቤት የሙስና ስጋት ተጋላጭ ከሚያደርጉ ጉዳዮች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ነው፡፡

ከታች የተያያዘዉ ሰንጠረዥ መ2 እንደሚያመለክተው አብዛኛው የጥናቱ ተሳታፊዎች በመስሪያ ቤታቸው ውስጥ በተለይም በተቋማት ፖሊሲና ስትራቴጅክ ዕቅዶች፣ ህግ መመሪያዎች እንዲሁም ወቅታዊ ዓመታዊ የተቋማት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች ላይ የመረጃ ግልፅነት እንዳለ ይስማማሉ:: ይሁን እንጅ ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ የጥናቱ ተሳታፊዎች በተለይም የፕሮጀክቶች አስተዳደር፣ የፕሮጀክቶች የበጀት መረጃ፣ ወቅታዊና ዓመታዊ የተቋማት ግዥ አፈፃፀም የመረጃ ግልፅነት የሌላቸው መሆናቸው ተመላክቷል:: በሌላ በኩል ብዛት ያላቸው ተሳታፊዎች በአንዳንድ መረጃዎች ማለትም በገለልተኛ አካል የተመዘነ ዓመታዊ የደንበኛ እርካታ ሪፖርት፣ የፕሮጀክቶች አስተዳደር እንዲሁም ተቋማት በሚያስወግዱት ንብረቶች ላይ የመረጃ ግልጽነት ይኑር ወይም አይኑር የሚያውቁት ነገር እንደሌለ አመላክተዋል::

የስነምግባር ክፍልን አቅምና ብቃት ማሳደግ ተቋማት የሙስና ስጋት ተጋላጭነትን ለመቀነስ የሚያደርጉትን ትግል የተሳካና ውጤታማ ከሚያደርጉ ድርጊቶች ውስጥ ዋነኛው ነው:: በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ ተቋማት የስነምግባር መከታትያ ክፍላቸውን አቅምና ጉልበት ለማሳደግ እያደረጉት ያለዉን ጥረት ተሳታፊዎች እንዴት እንደሚመለከቱት የሚዳስስ ስራ ተከናውኗል (አባሪ ሰንጠረዥ መ3 ይመልከቱ)::

በተቋማት ውስጥ ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል በሚያደርጉት ጥረት ታማኝነት ያለዉ መረጃ የማመንጨት አቅምና ብቃታቸውን ማሳደግ ይጠበቅባቸዋል:: በመሆኑም ይህ ጥናት ተሳታፊዎች ተቋማት ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ታማኒነት ያለው መረጃ የማመንጨት ብቃታቸውን እንዲገመግሙ በተጠየቁት መሰረት አብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች ተቋማት ያላቸዉ መረጃ የማመንጨት አቅምና ብቃት የሚፈለገዉ ደረጃ ላይ አለመድረሱን የተተነተነው መረጃ ያሳያል:: ከጥናቱ ተሳታፊዎች መካከል የማይናቅ አሃዝ ያላቸ ተሳታፊዎች (28 በመቶ የሚሆኑት) የተቋማት የበላይ አመራሮች ጥቆማዎችን የመቀበልና ውሳኔ የመስጠት ዝግጁነት፣ ተነሳሽነትና ተግባራዊ የማድረግ አቅም የላቸውም ወይም አቅማቸውን እንደማያውቁ የገለጹ ሲሆን ተቋማት የሙስናና ብልሹ ተግባራት ጥቆማዎችን በማደራጀት ለኮሚሽኑ የማቅረብ አቅምና ብቃታቸዉም ከሚፈለገው ደረጃ የደረሰ አለመሆኑን አመላክተዋል:: በሌሎች ተዛማጅ መረጃዎች ላይም የተሳታፊዎች መልስ ተቋማት በዚህ ረገድ ብዙ ስራ እንደሚጠበቅባቸው አመላካች ነው(አባሪ ሰንጠረዥ መ5 ይመልክቱ)::

የሙስና ምልክቶችን ለሚመለከተው አካል መጠቆምን በተመለከተ 74 በመቶ የሚሆኑት የዳሰሳ ጥናት ተሳታፊዎች በተቋማቸው ውስጥ ለተከሰቱ የሙስና አይነቶች ለሚመለከተው አካል ጥቆማ አለመደረጉን አመላክተዋል:: ለጥቆማው አነስተኛነት ምክንያት ከሆኑ ነገሮች ውስጥ ሰዎች ጥቆማ ቢሰጡም የሚመለከተዉ አካል ተገቢዉን እርምጃ በተገቢዉ ጊዜ ስለማይሰጥ (49%)፣ ለጠቋሚዎቹ ከለላ ስለማይደረግ ጥቃት ይደርስብናል ብለዉ ስለሚያምኑ (23%) እንዲሁም በማህበረሰቡ ዉስጥ ሙስና የተለመደ የአሰራር ልምድ ስለሆነ ጥቆማ አያስፈልግም የሚል ግንዛቤ ስላለ (15%) መሆኑን በተሳታፊዎች ከተጠቀሱ ምክናያቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው:: የሙስና ጥቆማ ከሰጡ ግለሰቦች መካከል ቁጥሩ ቀላል የማይባል ጥቆማ ከተቋሙ ሰራተኞች መምጣቱ ሙስናን የሚጠየፍ ማህበረሰብ ከመፍጠር አኳያ አበረታች እንቅስቃሴ

ስለሆነ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ሊበረታቱና የህግ ከለላን ጨምሮ ሌሎች ድጋፎች ሊደረጉላቸው ይገባል። በሌላ በኩል አብላጫ አሃዝ ያለው የጥናቱ ተሳታፊ (ወደ 51 በመቶ የሚሆነው) የሙስና ጥቆማዎች ተገቢውን መልስ አግኝተዋል ብለው እንደማያምኑ አመላክተዋል (ሰንጠረዥ መ6ን ይመልከቱ)። በተጨማሪም የጥናቱ ተሳታፊዎች ይህ መጠይቅ እስከ ተካሄደበት ድረስ ብዛት ያላቸው ጥቆማዎች መልስ እንዳላገኙና መልስ የተሰጣቸውም ቢሆኑ ጥቆማዎቹ ከተሰጡ የዘገየ ስለነበር አስተማሪነቱ ከዚህ ግባ የሚባል አይደለም የሚል ግንዛቤ አላቸው።

ሰንጠረዥ መ6፡ በትምህርት ተቋማት አገልግሎትን በተመለከተ የሙስና ስጋት ጥናት ተሳታፊዎች መልስ

<table>
<tr><th rowspan="2">ተ.ቁ</th><th rowspan="2" colspan="3">ጥያቄ</th><th colspan="3">መግለጫ በመቶኛ</th></tr>
<tr><th>አዎ</th><th>የለም</th><th>ድምር</th></tr>
<tr><td>1</td><td colspan="3">በተቋሙ ዙሪያ የመልካም አስተዳደር ችግሮች አሉ ብለው ያስባሉ?</td><td>64.7</td><td>34.5</td><td>99.2</td></tr>
<tr><td>2</td><td colspan="3">በተቋሙ ዙሪያ የሙስና ችግሮች አሉ ብለው ያስባሉ?</td><td>66.4</td><td>32.7</td><td>99.1</td></tr>
<tr><td>3</td><td colspan="3">ለጥያቄ 61 መልስዎ የለም ከሆነ በተቋሙ ውስጥ ለሙስና ተጋላጭ ሊሆኑ ይችላሉ ብለዉ የሚያስቧቸዉ የስራ ክፍሎች አሉ?</td><td>67.1</td><td>31.8</td><td>99</td></tr>
<tr><td>4</td><td colspan="3">በተቋሙ ዉስጥ ለተከሰቱ የሙስና አይነቶች ለሚመለከተው አካል ጥቆማ አለ?</td><td>26.1</td><td>73.5</td><td>99.6</td></tr>
</table>

<table>
<tr><td rowspan="2">5</td><td rowspan="2">ጥቆማዎቹ በአብዛኛዉ የሚመጡት ከየት ነዉ ?</td><td colspan="2">በተቋሙ ሰራተኞች</td><td>ከተቋሙ ሰራተኞች ዉጭ በሆኑ አካላት</td><td colspan="3">ሌላ ካለ _በዝርዝር ይጻፉ</td></tr>
<tr><td colspan="2">47.4</td><td>20</td><td colspan="3">1.5</td></tr>
<tr><td rowspan="2">6</td><td rowspan="2">ጥቆማዎቹ ያልተሰጡት በእርስዎ እምነት ለምን ይመስለዎታል?</td><td colspan="2">ሰዎች ጥቆማ ቢሰጡም የሚመለከተዉ አካል ተገቢዉን እርምጃ በተገቢዉ ጊዜ ስለማይሰጥ</td><td>ለጠቋሚዎቹ ከለላ ስለማይደረግ ጥቃት ይደርስብናል ብለዉ ስለሚያምኑ</td><td colspan="2">በማህበረሰቡ ዉስጥ ሙስና የተለመደ የአሰራር ልምድ ስለሆነ ጥቆማ አያስፈልግም የሚል ግንዛቤ ስላለ</td><td>ሌላ ካለ _በዝርዝር ይጻፉ</td></tr>
<tr><td colspan="2">48.6</td><td>22.8</td><td colspan="2">14.9</td><td>2.9</td></tr>
<tr><td rowspan="2">7</td><td rowspan="2">ጥቆማዎቹ ተገቢዉን መልስ አግኝተዋል ብለዉ ያስባሉ?</td><td colspan="2">አዎ</td><td>የለም</td><td colspan="3">ድምር</td></tr>
<tr><td colspan="2">27.8</td><td>51.5</td><td colspan="3">79.3</td></tr>
<tr><td rowspan="2">8</td><td rowspan="2">ለጥቆማዎቹ የተሰጠዉ መልስ በእርስዎ አስተያየት ምን መሆን ነበረበት ብለዉ ያምናሉ?</td><td colspan="2">ከወንጀሉ ጋር የማይጣጣም አነስተኛ ቅጣት ተሰጥቷል</td><td>ከወንጀሉ ጋር የማይጣጣም ከፍተኛ ቅጣት ተሰጥቷል</td><td colspan="2">ከወንጀሉ አኳያ ምንም ቅጣት አልተሰጠም</td><td>ሌላ ካለ በዝርዝር ይጻፉ</td></tr>
<tr><td colspan="2">22.4</td><td>7</td><td colspan="2">37</td><td>1.9</td></tr>
<tr><td rowspan="2">9</td><td rowspan="2">ጥቆማዎቹ ተገቢዉን መልስ በተገቢዉ ጊዜ አግኝተዋል ብለዉ ያስባሉ?</td><td colspan="2">አዎ</td><td>የለም</td><td colspan="3">ድምር</td></tr>
<tr><td colspan="2">29.2</td><td>41..6</td><td colspan="3">70.8</td></tr>
<tr><td rowspan="2">10</td><td rowspan="2">ጥቆማዎቹ መልስ ያገኙት መቼ ነዉ?</td><td>በጣም ዘግይቶ</td><td>ዘግይቶ</td><td>በፍጥነት</td><td>በጣም በፍጥነት</td><td>የተሰጠ መልስ አላየሁም</td><td>ሌላ ካለ በዝርዝር ይጻፉ</td></tr>
<tr><td>14.7</td><td>11.4</td><td>4.6</td><td>1.9</td><td>30.5</td><td>1.4</td></tr>
<tr><td rowspan="2">11</td><td rowspan="2">ሙስናን ለመከላከል ከተቋቋሙት አካላት በእርስዎ እምነት ሙስናን ለመከላከል ምን መደረግ አለበት ብለዉ ያስባሉ?</td><td colspan="2">የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ለህብረተሰቡ በሰፊዉ መስጠት</td><td>በሙሰኞች ላይ ህጉ በሚፈቅደዉ መሰረት ተመጣጣኝ እርምጃ በተገቢዉ ጊዜ መዉሰድ ተችሏል።</td><td>አሁን በስራ ላይ ያለዉ ህግ የላላ ስለሆነ ጠበቅ ያለ ህግ አዉጥቶ ማስፈፀም</td><td colspan="2">ሌላ ካለ _በዝርዝር ይጻፉ……………………………</td></tr>
<tr><td colspan="2">39.1</td><td>36.1</td><td>20.5</td><td colspan="2">3.4</td></tr>
<tr><td rowspan="2">12</td><td rowspan="2">በተቋምዎ ዉስጥ በሚካሄዱ የግዥ ሂደቶች የሙስና ትጋላጭነትና ስጋት አለ ብለዉ ያምናሉ?</td><td colspan="3">አዎ</td><td>የለም</td><td colspan="2">ድምር</td></tr>
<tr><td colspan="3">58.8</td><td>39.6</td><td colspan="2">98.5</td></tr>
<tr><td>13</td><td>በተቋምዎ ዉስጥ የሙያ ፈቃድ አሰጣጥ፣ እድሳትና ስረዛ ስራዎች ይከናወናሉ?</td><td colspan="3">37.8</td><td>61.3</td><td colspan="2">99.1</td></tr>
<tr><td>14</td><td>በተቋምዎ ዉስጥ የግንባታ ስራዎች ወይም የህንፃዎች እድሳት ይከናወናል?</td><td colspan="3">68.8</td><td>30.6</td><td colspan="2">99.4</td></tr>
</table>

ክፍል 4፡ የሙስና ስጋት ምዘናና ግምገማ

በዚህ ክፍል ውስጥ የሚካተቱት አበይት ተግባራት መካከል የሙስና ስጋቶችን የመመዘንና የሚያስከትሉትን ተጽዕኖ መገምገም ይሆናል፡፡ ስለሆነም የጥናቱ ተሳታፊዎች በተቋማት ውስጥ የሙስና ስጋት አለባቸው ብለው የለዩአቸውን የስራ ሂደቶች፣ የሙስና ስጋቶችን፣ ስጋቶቹ የመከሰት ዕድላቸውንና ቢከሰቱ ሊያስከትሉ የሚችሉትን ተጽዕኖ በመተንተን ለሙስና ስጋቶች የምዘናና ግምገማ ተግባራት የተከናወኑ ሲሆን በመጨረሻም ለሙስና ስጋቶች ደረጃ በማዉጣት ተቋማት ወደፊት ትኩረት ሰጥተው ሊያከናዉኗቸው የሚገቡትን ተግባራት የመጠቆም ስራዎችን ያካትታል፡፡

4.1. በሁሉም የትምህርት ተቋማት የሙስና ስጋት ምዘና

በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ የትምህርት ተቋማት መደበኛ ስራቸውን ሲያከናዉኑ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስና ስጋቶችን የመለየትና የመከሰት ዕድላቸዉን በቅደም ተከተል የማስቀመጥ ስራ ይከናወናል፡፡ በመቀጠልም የመከሰት ዕድላቸዉንና ቢከሰቱ ሊያስከትሉት የሚችሉትን ተጽዕኖ በደረጃ በማስቀመጥ በመጨረሻም የሙስና ግምገማ የማካሄድ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

በተቋማት የሚታዩ ስጋቶች፡- በዚህ የጥናት ሰነድ በክፍል ሶስት ውስጥ እንደቀረበውና አሁንም በአሃዛዊ መረጃ እንደታየው በተለያዩ የትምህርት ተቋማት ውስጥ ብዛት ያላቸው የሙስና ስጋቶች የተለዩ ሲሆን የመከሰት ዕደላቸውም በቅደም ተከተል ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ በመሆኑም ከሁሉም ተቋማት ከ20 በላይ የሙስና ስጋቶች የተለዩ ሲሆን የመምህራን በተደጋጋሚ ክፍል አለመግባት፣ ህገወጥ ቅጥር፣ ዝዉዉር እና ደረጃ ዕድገት፣ የአሰራር ግልጽነት መጓደል እና ግዥዎች ህግና ደንብን ተከትለዉ አለመከናዎን ከተጠቀሱት ስጋቶች ውስጥ የመከሰት ዕድላቸው ሰፊ የሆነና የመጀመሪያውን ከአንድ እስከ አራት ደረጃ የያዙ ናቸው (ለበለጠ መረጃ ሰንጠረዥ ሠ1 ይመልከቱ)፡፡

የሙስና ስጋቶች የመከሰት ዕድል በደረጃ፡- የሙስና ተጋላጭነት ስጋቶች የመከሰት ዕድል በሶስት ደረጃ የተከፈለ ሲሆን እነሱም ዝቅተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ በመባል እንደገና በደረጃ ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ በመሆኑም የመምህራን በተደጋጋሚ ክፍል አለመግባት፣ ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ መስጠት፣ በአመራሩ የሚከናወን ስርቆት፣ ህገወጥ ቅጥር፣ ዝዉዉርና ደረጃ ዕድገት እና ግዥዎች ህግና ደንብን ተከትለዉ አለመከናዎን ከሙስና ስጋቶች ውስጥ ከፍተኛ የመከሰት ዕድል ያላቸው ስጋቶች በመሆን ተጠቅሰዋል፡፡ በሌላ በኩል በሌሉ ሰራተኞች ስም ደመውዝ መክፈል ወይም መዉሰድ፣ በመዝገብ ወይም ሬጅስተራር ቤት በኩል ያላለፉ ተማሪዎችን እንዳለፈ ተደርጎ ሰርተፊኬት መስጠት እና ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ሄደው እንዲማሩ ማድረግ፣ሁለት ቦታ ላይ ደመዎዝ መዉሰድ፣ ለተማሪ የማርክ ማጭበርበር መስራት፣ለስልጠና የሚያዘዉ በጀት ሚዛናዊ አለመሆን እና ለስልጠና መስተንግዶ የሚያዘዉ በጀት የተጋነነ መሆን ዝቅተኛ የመከሰት ዕድል ያላቸው የሙስና ስጋቶች ናቸው፡፡ ሌሎች በሰንጠረዝ ሠ1 የተመለከቱት የሙስና ስጋቶች መካከለኛ የመከሰት ዕድል ያላቸው ናቸው፡፡

የሙስና ስጋቶች ቢከሰቱ የሚያደርሱት ተጽዕኖ፡- የሙስና ስጋቶች ቢከሰቱ ሊያደርሱ የሚችሉት ተጽዕኖ የመረጃ ትንተና የተካሄደ ሲሆን ከስጋቶች ውስጥ የመምህራን በተደጋጋሚ ክፍል አለመግባት፣ህገወጥ

ቅጥር፣ ዝዉዉርና የደረጃ ዕድገት፣ በአመራሩ የሚከናወን ስርቆት እና ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ መስጠት ቢከሰቱ አደገኛ ተጽዕኖ ሊያስከትሉ ይችላሉ ተብለው ከአንደኛ እስከ አራተኛ የተዘረዘሩ ስጋቶች ናቸዉ። በሌላ በኩል ሁለት ቦታ ላይ ደመዎዝ መዉሰድ፣ በሌሉ ሰራተኞች ስም ደመዎዝ መክፈል ወይም መዉሰድ እና ለስልጠና መስተንግዶ የሚያዘዉ በጀት የተጋነነ መሆን ቢከሰቱ የተጋነነ ተጸዕኖ ሊያስከትሉ የማይችሉ ስጋቶች መሆናቸዉን በጥናቱ ተሳታፊዎች ተመላክቷል።

የሙስና ስጋቶች የሚያደርሱት ተጽዕኖ በደረጃ፡- የሙስና ስጋቶች የመከሰት ዕድል በሶስት ደረጃ የተከፈለ ሲሆን እነሱም አነስተኛ፤ መጠነኛ እና ከባድ ተጽዕኖ በመባል እንደገና በደረጃ ለማስቀመጥ ተሞክሯል። በመሆኑም የመምህራን በተደጋጋሚ ክፍል አለመግባት፤ በመዝገብ ወይም ሬጅስተራር ቤት በኩል ያላለፉ ተማሪዎችን እንዳለፈ ተደርጎ ሰርትፊኬት መስጠት አና ወደሌላ ት/ቤት ሄደው እንዲማሩ ማድረግ፤ ሁለት ቦታ ላይ ደመዎዝ መዉሰድ፤ለተማሪ የማርክ ማጭበርበር መስራት፤ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ መስጠት፤ በአመራሩ የሚከናወን ስርቆት፤ ህገወጥ ቅጥር፣ ዝዉዉር ና ደረጃ ዕድገት እና የአሰራር ግልጥነት መጓደል ቢከሰቱ ከባድ ተጽዕኖ የሚያስከትሉ ስጋቶች ሲሆኑ በሌሉ ሰራተኞች ስም ደመውዝ መክፈል ወይም መዉሰድ እና ለስልጠና መስተንግዶ የሚያዘዉ በጀት የተጋነነ መሆን ተብለው የተለዩ ስጋቶች ቢከሰቱ አነስተኛ ተጽዕኖ ሊያደርሱ የሚችሉ ስጋቶች ናቸው። ሌሎች የስጋት አይነቶች መካከለኛ ተጽዕኖ ሊያደርሱ የሚችሉ ተብለው ተመላክተዋል። ዝርዝር የተጽዕኖ ደረጃውን በሰንጠረዥ ሠ1 ላይ ይመልከቱ።

የሙስና ስጋቶች ግምገማ በደረጃ፡- የግምገማ ደረጃው የስጋቶች የመከሰት እድል በደረጃ እና ቢከሰቱ የሚያስከትሉት ተጽዕኖ በደረጃ ተባዝተው የሚሰጡት ውጤት ነው። የሙስና ግምገማ በሶስት ደረጃ የተከፈለ ሲሆን እነሱም አነስተኛ፤ መካከለኛና ከባድ በመባል በደረጃ ለማስቀመጥ ተሞክሯል። በመሆኑም የመምህራን በተደጋጋሚ ክፍል አለመግባት፤ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ መስጠት፤በአመራሩ የሚከናወን ስርቆት፤ ህገወጥ ቅጥር፣ ዝዉዉርና ደረጃ ዕድገት፤ ግዥዎች ህግና ደንብን ተከትለዉ አለመከናዎን፤ የመረጃና ማስረጃ ማጭበርበር እና የአሰራር ግልጥነት መጓደል ከባድ የሙስና ስጋት ደረጃ ያለቸው ናቸው። በሌላ መልኩ በሌሉ ሰራተኞች ስም ደመውዝ መክፈል ወይም መዉሰድ፤ ለስልጠና የሚያዘዉ በጀት ሚዛናዊ አለመሆን እና ለስልጠና መስተንግዶ የሚያዘዉ በጀት የተጋነነ መሆን አነስተኛ የስጋት ደረጃ ያላቸዉ የሙስና አይነቶች ናቸው። ሌሎች የስጋት አይነቶች መካከለኛ የስጋት ደረጃ ያለቸው የሙስና አይነቶች ናቸው። ዝርዝር የስጋት ደረጃውን በሰንጠረዥ ሠ1 ላይ ይመልከቱ።

ሰንጠረዥ ሠ1፡ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት አይነቶችና የተጽዕኖ ደረጃን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

ተ.ቁ	የሙስና ስጋት እና ተጋላጭነት አይነት	የሙስና ስጋት የመከሰት ዕድል ቅደም ተከተል	የመከሰት እድል በደረጃ			የሙስና ስጋት ቢከሰት ሊደርስ የሚችለው ጉዳት ቅደም ተከተል	የሙስና ስጋት ቢከሰት የሚያመጣው የተጽዕኖ ደረጃ			የሙስና ስጋት ደረጃ (የሙስና ስጋት የመከሰት ዕድል*የተጽዕኖ ደረጃ)	የስጋቱ መነስኤ	የስጋቱ መፍትሄ
			ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ		ከባድ	መጠነኛ	አነስተኛ			
1	የመምህራን በተደጋጋሚ ክፍል አለመግባት	1ኛ	✓			1ኛ	✓			ከባድ	• የሰራተኛው ዝቅተኛ የደሞዝ ክፍያ • የተጠያቂነት ስርዓት ውስንነት • የተጠናከረ የቁጥጥር ስርዓት አለመኖር	• የተጠናከረ እና ተከታታይነት ያለው የቁጥጥር ስርዓት ማስፈን • ተመጣጣኝ እና አስተማሪ የሆነ ቅጣት
2	በሌሉ ሰራተኞች ስም ደመውዝ መክፈል ወይም መዉሰድ	19ኛ			✓	18ኛ			✓	አነስተኛ		
3	በመዝገብ/ሬጅስተራር ቤት በኩል ያላለፉ ተማሪዎችን እንዳለፈ ተደርጎ ሰርትፊኬት መስጠት	16ኛ			✓	12ኛ	✓			መካከለኛ	• የሞራል መላሸቅ • ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት • የተጠያቂነት ስርዓት ወስንነት	• የተጠናከረ የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት ማስፈን • በአጥፊዎችን ላይ ተገቢውን ቅጣትመስጠት፡፡ • ክትትል እና ድጋፍ
4	ሁለት ቦታ ላይ ደመዎዝ መዉሰድ	18ኛ			✓	17ኛ	✓			መካከለኛ	• የተጠናከረ የቁጥጥር ስርዓት አለመኖር • ዝቅተኛ የደሞዝ • ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት	• የተጠናከረ የቁጥጥር ስርዓት ማስፈን • የተጠያቂነት ስርዓት ማስፈን • አስተማሪ ቅጣት መስጠት
5	ለተማሪ የማርክ ማጭበርበር መስራት	13ኛ			✓	10ኛ	✓			መካከለኛ	• የሞራል መላሸቅ • ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት • የፍታዊነትና የስነምግባር ጉድለት	• የተጠናከረ የቁጥጥር ስርዓት ማስፈን • አስተማሪ ቅጣት መስጠት
6	ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ መስጠት	10ኛ	✓			4ኛ	✓			ከባድ	• የሞራል መላሸቅ • ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት • በአቋራጭ ለመክበር • የተጠያቂነት ውስንነት	• ሁሉም የትምህርት ተቋማት የሁሉንም ተመራቂ መረጃ በኦንላይን ለህዝብ ይፋ ማድረግ፡፡ • የግንዛቤ ስራ መስራት • በአጥፊዎች ላይ የማያዳግም እርምጃ መውሰድ
7	በአመራሩ የሚከናወን ስርቆት	7ኛ	✓			3ኛ	✓			ከባድ	• የሞራል መላሸቅ • ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት • በአቋራጭ ለመክበር • የአሰራር ግንጽነት ማነስ	• ባለስልጣኑ እና ተራው ህዝብ እኩል የሚጠየቁበትን ህግ ማስፈን፡ : • ሁሉን አሰራር ግልጽና መመሪያ ተኮር ማድረግ
8	ህገወጥ ቅጥር፣ ዝዉዉር ና ደረጃ ዕድገት	2ኛ	✓			2ኛ	✓			ከባድ	• የሞራል መላሸቅ • ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት • በአቋራጭ ለመክበር • የአሰራር ግንጽነት ማነስ	• ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር ማስፈን • በአጥፊዎች ላይ አስተማሪና የማያዳግም እርምጃ መውሰድ • ጠንካራ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር

											• ፍታህዊነት የጎደለው አስተዳደር	ማድረግ
9	የመንግስትንና የህዝብን ንብረት ለግል ጥቅም ማዋል	5ኛ		✓		6ኛ		✓		መካከለኛ	• ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት • በአቋራጭ ለመክበር • የአሰራር ግንጽነት ማነስ • ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር አለመኖር	• በአጥፊዎች ላይ አስተማሪና የማያዳግም እርምጃ መውሰድ • ስራን በህግ፣ በግልጽነትና ተጠያቂነት መንፈስ መስራት • ጠንካራና ደፋር ማ/ሰብ መፍጠር
10	የተማሪ ዝዉዉርን በዘመድ አዝማድ እና በጥቅም መስራት	14ኛ		✓		16ኛ		✓		መካከለኛ	• ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት • የአሰራር ግንጽነት ማነስ	• ስራን በህግ፣ በግልጽነትና ተጠያቂነት መንፈስ መስራት
11	የት/ቤቱን የዉስጥ ገቢ እና ድጎማ አላግባብ ስራ ላይ ማዋል	9ኛ		✓		11ኛ		✓		መካከለኛ	• ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት • በአቋራጭ ለመክበር • የአሰራር ግንጽነት ማነስ	• ሃላፊዎች የሚጠየቁበትን የህግ ማዕቀፍ ማስፈን፡፡ • ሁሉን አሰራር ግልጽና መመሪያ ተኮር ማድረግ
12	የስልጠና ምልመላን በአግባቡ አለማከናዎን	6ኛ		✓		9ኛ		✓		መካከለኛ	• ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት • ፍታዊ ያልሆነ እና አድሎአዊ አስተዳደር/አሰራር	• ለሁሉም ሰራተኞች ፍታዊነት ያለው አገልግሎት መስጠት • ግልጽነትና ተጠያቂነት
13	የስልጠና የሚያዘዉ በጀት ሚዛናዊ አለመሆን	11ኛ			✓	15ኛ		✓		አነስተኛ		
14	የተጋነነ የአበል አከፋፈል	12ኛ		✓		14ኛ		✓		መካከለኛ	• ሃላፊነትን በአግባቡ አለመወጣት • የአመራሩ ልል መሆን	• ግልጽነትና ተጠያቂነት
15	ለስልጠና መስተንግዶ የሚያዘዉ በጀት የተጋነነ መሆን	17ኛ			✓	19ኛ			✓	አነስተኛ		
16	ግዥዎች ህግና ደንብን ተከትለዉ አለመከናዎን	4ኛ	✓			7ኛ	✓			ከባድ	• የተጠናከረ የቁጥጥር ስርዓት አለመኖር • ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት • በአቋራጭ ለመክበር • የአመራሩ ልል መሆን • የግዥ ጨረታ ሰነድ ግልጽነት ማነስ እና ደራሽ የሆነ ግዥ	• መመሪያና ደንብን በአግባቡ ጠንቅቆ ማሳወቅ እና መተግበር • ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማስፈን • ጠንካራ የሆነ የቁጥጥርና ክትትል ማድረግ እና በአጥፊዎች ላይ አስተማሪ የሆነ ቅጣት መስጠት • ፈጻሚ አካላት በእቅድ እንዲመሩ ማድረግ
17	የመረጃና ማስረጃ ማጭበርበር	15ኛ		✓		13ኛ	✓			ከባድ	• ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት • በአቋራጭ ለመክበር • ስግብግብለነትና ሉሰኝነት • የስነ ምግባር ጉድለት	• በመረጃዎች ላይ ጠንካራ የሆነ የክትትልና ቁትጥር ስርዓት ማስፈን፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት • የተቋማቱን መረጃ በተሟላ ሁኔታ መያዝ
18	የተመደበ በጀት ለታለመለት ዓላማ አለመዋል	8ኛ		✓		8ኛ		✓		መካከለኛ	• ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት • በአቋራጭ ለመክበር • ግልጽነትና ተጠያቂነት አለመኖር	• ስራን በግልጽነትና ተጠያቂነት መስራት • በእቅድ መመራት
19	የአሰራር ግልጥነት መጓደል	3ኛ		✓		5ኛ	✓			ከባድ	• የአመራሩ ልል መሆን እና ሃላፊነትን በአግባቡ አለመወጣት	• ስራን ብህጉ መሰረት ግልጽነትና ሃላፊነት ባለው መልኩ መስራት
20	ሌላ ካለ _በዝርዝር ይጻፉ	20ኛ			✓	20ኛ			✓	አነስተኛ		

4.2. ለሙስና ተጋላጭ ተደርገው በሚወሰዱ የስራ ክፍሎች ላይ የስጋት ምዘና

በትምህርት ተቋማት ውስጥ ከሚገኙ የስራ ክፍሎች ውስጥ ሙስና በስፋት ሊገኝባቸው ይችላሉ ተብለው የተገመቱ የስራ ክፍሎች ተለይተዋል፡፡ በነዚህ የስራ ክፍሎች ውስጥ የሚታየው የሙስና ስጋት፣ የስጋቱ የመከሰት እድልና ቢከሰት የሚያደርሰው የተፅዕኖ ደረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ለሙስና እና ለብልሹ አሰራር ሊጋለጡ የሚችሉ የስራ ክፍሎች፡- የጥናት ተሳታፊዎች በትምህርት ተቋማት ውስጥ ለሙስናና ብልሹ አሰራር ሊጋለጡ የሚችሉ የስራ ክፍሎች እንዲለዩ ብሎም የመከሰት ዕድላቸውን በቅደም ተከተል እንዲገልጹ በተጠየቁት መሰረት በትምህርት ተቋማት ለሙስናና ብልሹ አሰራር ሊጋለጡ ይችላሉ የተባሉ ስምንት የስራ ክፍሎች የተለዩ ሲሆን የሙስና ስጋት ሊከሰትባቸው የሚችል ዕድልም በቅደም ተከተል ለማስቀመጥ ተሞክሯል (ሰንጠርዥ ረ1ን ይመልከቱ)፡፡ ከስምንቱ የስራ ክፍሎች መካከል ግዥ፣ ፋይናንስ፣ የሰው ሃብት ልማት እና ንብረት ክፍሎች ለሙስና የመጋለጥ ከፍተኛ ዕድል ያላቸው ተብለው ከአንድ እስከ አራት በቅደም ተከተል የተቀመጡ የስራ ክፍሎች ናቸው፡፡ ስለሆነም የትምህርት ተቋማት በአጠቃላይ እንዲሁም የሥነምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን በተለይ ተቋማት ካሏቸው የስራ ክፍሎች ሙስና የመከሰት ዕድል ሰፊ የሆነባቸውን በመለየትና ወደፊት ቢቻል ለሙስና በር የማይከፍቱበትን፤ ካልተቻለ ደግሞ ሙስና የመከሰት ዕድልን ወደ ዜሮ ለማዉረድ ስትራቴጅ ነድፈው መንቀሳቅስ ይኖርባቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ሬጅስትራር፣ መዝገብ ቤት ወይም መረጃ ክፍል እና ማህበረሰብ አገልግሎትና ምርምር ክፍሎች ሙስና የመከሰት ዕድሉ አሳሳቢ ያልሆነባቸው የስራ ክፍሎች እንደሆኑ ተመላክቷል (ዝርዝር መረጃዉን በሰንጠውረዥ ረ1 ላይ ይመልከቱ)፡፡

ለሙስና እና ለብልሹ አሰራር ሊጋለጡ የሚችሉ የስራ ክፍሎች በደረጃ፡-ለሙስና እና ብለሹ አሰራር ተጋላጭ ሊሆኑ የሚችሉ የስራ ክፍሎች እና በውስጣቸው ሙስና የመከሰት ያለው ዕድል በሶስት ደረጃ የተከፈለ ሲሆን እነሱም ዝቅተኛ፤ መካክለኛ እና ከፍተኛ በመባል እንደገና በደረጃ ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ በመሆኑም ግዥ ክፍል ውስጥ ሙስና ከፍተኛ የመከሰት ዕድል ያለው በመሆን ተጠቅሷል፡፡ በሌላ በኩል መማርና ማስተማር፤ ማህበረሰብ አገልግሎት እና ምርምር እና መዝገብ ቤት / መረጃ ክፍሎች ሙስና ዝቅተኛ የመከሰት ዕድል ያለው በመባል ተጠቅሰዋል፡፡ ሌሎች በስንጠረዝ ረ1 የተመለከቱት የስራ ክፍሎች ሙስና መካከለኛ የመከሰት ዕድል ያላባቸው የስራ ክፍሎች ናቸው፡፡

ሙስና ቢከሰት የሚያስከትለው ተጽዕኖ፡- ለሙስናና ብልሹ አሰራር ሊጋለጡ የሚችሉ የስራ ክፍሎችና በዉስጣቸው ሙስና ቢከሰት ሊያስከትል የሚችለውን ተጽዕኖ የመረጃ ትንተና የተካሄደ ሲሆን ከስራ ክፍሎች ውስጥ ግዥ፤ ፋይናንስ፤ የሰው ሀብት ልማት እና ንብረት ክፍሎች ሙስና ቢከሰት አደገኛ ተጽዕኖ ሊያስከትል ይችላል ተብለው ከአንደኛ እስከ አራተኛ የተዘረዘሩ የስራ ክፍሎች ናቸዉ፡፡ በሌላ በኩል ረጅስትራር፤ መዝገብ ቤት/መረጃ እና ማህበረሰብ አገልግሎትና ምርምር የስራ ክፍሎች ሙስና ቢከሰት አሳሳቢ ተጽዕኖ የማያስከትልባቸው የስራ ክፍሎች መሆናቸዉን በጥናቱ ተሳታፊዎች ተመላክቷል፡፡

ሙስና ቢከሰት የሚያስከትለው ተጽዕኖ በደረጃ፡- በተቋማት ለሙስናና ብልሹ አሰራር ሊጋለጡ በሚችሉ የስራ ክግሎች ውስጥ ሙስና ቢከሰት የሚያስከትለዉ ተጽዕኖ በሶስት ደረጃ የተከፈለ ሲሆን እነሱም አነስተኛ፤ መጠነኛ እና ከባድ ተጽዕኖ በመባል እንደገና በደረጃ ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ በመሆኑም ግዥ፤ ማህበረሰብ አገልግሎትና ምርምር፤ የሰዉ ሃብት ልማትና አስተዳደር እና ረጅስትራር የስራ ክፍሎች ውስጥ ሙስና ቢከሰት ከባድ ተጽዕኖ የሚያስከትል ሲሆን በመማርና ማስተማር የስራ ክፍል ሙስና ቢከሰት አነስተኛ ተጽዕኖ ሊኖረው እንደሚችል ተመላክቷል፡፡ ሌሎች የስራ ክፍሎች ሙስና ቢከሰት መካከለኛ ተጽዕኖ ሊያደርስ የሚችልባቸው ተብለው ተመላክተዋል፡፡ ዝርዝር የተጽዕኖ ደረጃውን በሰንጠረዥ 21 ላይ ይመልከቱ፡፡

የሙስና ስጋት ምዘና በደረጃ፡- የስራ ክፍሎች የሙስናና ብልሹ አሰራር ተጋላጭነት ግምገማ በሶስት ደረጃ የተከፈለ ሲሆን እነሱም አነስተኛ፤ መካከለኛና ከባድ በመባል በደረጃ ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ የግምገማ ደረጃው የሙስና የስራ ክፍሎች የመከሰት እድል በደረጃ እና ቢከሰት የሚያስከትለው ተጽዕኖ በደረጃ ተባዝተው የሚሰጡት ውጤት ነው፡፡ በመሆኑም ግዥ፤ የሰዉ ሃብት ልማትና አስተዳደር እና ረጅስትራር የስራ ክፍሎች ከባድ የሆነ የሙስና ስጋት ያለባቸው የስራ ክፍሎች ሲሆኑ መማር ማስተማር እና መዝገብ ቤት/መረጃ የስራ ክፍሎች አነስተኛ የሆነ የሙስና ስጋት ያለባቸው ክፍሎች ናቸዉ፡፡ ሌሎች የስራ ክፍሎች መካከለኛ የሆነ የሙስና ስጋት ያለባቸው የስራ ክፍሎች ናቸው፡፡ ዝርዝር የተጽዕኖ ደረጃውን በሰንጠረዥ 21 ላይ ይመልከቱ፡፡

ሰንጠረዥ ፬1፡ ለሙስና እና ለብልሹ አሰራር ሊጋለጡ የሚችሉ የስራ ክፍሎች ትንተና እና የተጸዕኖ ደረጃ

ተ.ቁ	ለሙስና እና ለብልሹ አሰራር ሊጋለጡ የሚችሉ አሰራሮች	የሙስና ስጋት የመከሰት ዕድል ቅደም ተከተል	የመከሰት እድል በደረጃ			የሙስና ስጋት ቢከሰት ሊደርስ የሚችለውጉዳት ቅደም ተከተል	የሙስና ስጋት ቢከሰት የሚያመጣው የተጽዕኖ ደረጃ			የሙስና ስጋት (የሙስና ስጋት የመከሰት ዕድል*የተጽዕኖ) ደረጃ	የስጋቱ መንስኤ	የስጋቱ መፍትሄ
			ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ		ከባድ	መጠነኛ	አነስተኛ			
1	ግዥ ክፍል	1ኛ	✓			1ኛ	✓			ከባድ	• በግዥ ሂደት የሙስናና ብልሹ አሰራር አመለካከት መኖር • የግዥ መዘግየትና የጨረታ ሰነድ ግልጽነት ማነስ • የሚጠየቁ የግዥ ጥያቄዎች ደራሽ መሆናቸው	• የተጠናከረ ቁጥጥርና ክትትል • ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር ማስፈን • ፈጻሚ አካላት በእቅድ በቻ ግዥ እንዲፈጽሙ ማድረግ • ለአጥፊዎች ተገቢ ቅጣት መስጠት
2	መማርና ማስተማር	5ኛ			✓	5ኛ			✓	አነስተኛ		
3	ማህበረሰብ አገልግሎት እና ምርምር	8ኛ			✓	8ኛ	✓			መካከለኛ	• ከፍተኛ የሆነ በጀት መኖር • ግልጽና የተጠናከር የቁጥጥር እና ክትትል ስርዓት አለመኖር • መመሪያና ደንብን አለማወቅ • ማበረታቻ አለመኖር	• ሁሉም አሰራር መመሪያ ተኮር መሆን አለበት • ጠንካራ የሆነ የቁጥጥር ስርዓት • ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማስፈን • ጠንካራ የሆነ የህግ ስርዓት
4	ፋይናንስ ክፍል	2ኛ		✓		2ኛ		✓		መካከለኛ	• ግልጽና የተጠናከር የቁጥጥር እና ክትትል ስርዓት አለመኖር • መመሪያና ደንብን አለማወቅ	• ሁሉም አሰራር መመሪያ ተኮር • ጠንካራ የሆነ የቁጥጥር ስርዓት • ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማስፈን
5	ንብረት ክፍል	3ኛ		✓		4ኛ		✓		መካከለኛ	• ግልጽና የተጠናከር የቁጥጥር እና ክትትል ስርዓት አለመኖር	• ጠንካራ የሆነ የቁጥጥር ስርዓት • ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማስፈን
6	መዝገብ ቤት / መረጃ ክፍል	7ኛ			✓	7ኛ		✓		አነስተኛ		
7	የሰው ሃብት አስተዳደር ክፍል	4ኛ		✓		3ኛ	✓			ከባድ	• የአመራር ልል መሆን • የህግ መላላት • መመሪያና ደንብን በአግባቡ ጠንቅቆ አለማወቅ • የግልጽነትና ተጠያቂነት ሰርዓት ውስንነት	• አጥፊዎችን አጋልጦ ለፍትህ ማቅረብ • ሁሉትም አሰራር መመሪያ ተኮር • ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ማስፈን • ስራና ፖለቲካን መለየት
8	ሬጂስትራር	6ኛ		✓		6ኛ	✓			ከባድ	• ጠንካራ የሆነ የቁትጥር ስርዓት አለመኖር • የተጠያቂነት ስርዓት አለመኖር	• በአጥፊዎች ላይ እርምጃ መውስድ • ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማስፈን • ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ
9	ሌላ ካለ በዝርዝር ይጻፉ	9ኛ			✓	9ኛ			✓	አነስተኛ		

4.3. በትምህርት ተቋማት ውስጥ በሚገኙ ግዥ ክፍሎች ውስጥ የስጋት ምዘና

በዚህ ንዕስ ክፍል በትምህርት ተቋማት ውስጥ በሚካሄዱ የግዝ ሂደቶች የሙስና ስጋቶችን የመለየትና የመከሰት ዕድላቸዉን በቅደም ተከተል የማስቀመጥ ስራ እንዲሁም የመከሰት ዕድላቸዉንና ቢከሰቱ ሊያስከትሉት የሚችሉትን ተጽዕኖ በደረጃ ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡

የሙስና ስጋት ትንተና፡- በትምህርት ተቋማት ውስጥ በሚካሄዱ የግዥ ሂደቶች ያለዉን የሙስና ስጋት ለመለየትና የመከሰት ዕድላቸውን በቅደም ተከተል ለማስቀመት እንዲረዳ በግዥ ሂደት ሊከሰቱ የሚችሉ አምስት የሙስና ስጋቶች የመለየትና የስጋቶቹን የመከሰት ዕድልም በቅደም-ተከተል ለማስቀመጥ ተሞክሯል (ሰንጠርዥ ሸ1ን ይመልከቱ)፡፡ እነዚህ ስጋቶች በግዥ በጀት ዝግጅት ወቅት (ለተቋሙ የማያስፈልግ ዕቃ እንዲገዛ በጀት እንዲያዝ በማድረግ)፣ በጨረታ ሰነድ ዝግጅት ወቅት (የተወሰኑ ተወዳዳሪዎችን በተለየ ሁኔታ እንዲጋብዝ አድርጎ ማዘጋጀት) እና በጨረታ ሰነድ የቴክኒክ ግምገማ ወቅት የሚከሰቱ የሙስና ስጋቶች ከፍተኛ ዕድል ያላቸው ተብለው ከአንድ እስከ ሶስት በቅደም ተከተል የተቀመጡ ስጋቶች ናቸው፡፡

የሙስና ስጋቶች የመከሰት ዕድል በደረጃ፡- በትምህርት ተቋማት በሚካሄዱ የግዥ ሂደቶች ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስና ተጋላጭነትና ስጋቶችን እና የመከሰት ዕድላቸው በሶስት ደረጃ የተከፈለ ሲሆን እነሱም ዝቅተኛ፤ መካከለኛ እና ከፍተኛ በመባል እንደገና በደረጃ ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ በመሆኑም በግዥ በጀት ዝግጅት ወቅት (ለተቋሙ የማስፈልግ ዕቃ እንዲገዛ በጀት እንዲያዝ በማድረግ)፤ በጨረታ ሰነድ ዝግጅት ወቅት (የተወሰኑ ተወዳዳሪዎችን በተለየ ሁኔታ እንዲጋብዝ አድርጎ ማዘጋጀት) እና በጨረታ ሰነድ የፋይናንስ ግምገማ ወቅት ሙስና ከፍተኛ የመከሰት ዕድል ያለው በመሆን ተጠቅሷል፡፡ በሌላ በኩል በጨረታ ሰነድ የቴክኒክ ግምገማ ወቅት የሙስና ስጋት ያለዉ የመከሰት ዕድል መካከለኛ እንደሆነ ተመላክቷል፡፡

ሙስና ቢከሰት የሚያስከትለው ተጽዕኖ፡- በትምህርት ተቋማት ውስጥ በሚደረጉ የግዥ ሂደቶች ውስጥ ሙስና ቢከሰት ሊያስከትል የሚችለውን ተጽዕኖ የመረጃ ትንተና የተካሄደ ሲሆን ከስጋቶቹ ውስጥ በግዥ በጀት ዝግጅት ወቅት (ለተቋሙ የማያስፈልግ ዕቃ እንዲገዛ በጀት እንዲያዝ በማድረግ)፤ በጨረታ ሰነድ ዝግጅት ወቅት (የተወሰኑ ተወዳዳሪዎችን በተለየ ሁኔታ እንዲጋብዝ አድርጎ ማዘጋጀት) እና በጨረታ ሰነድ የቴክኒክ ግምገማ ወቅት የሚከሰቱ የሙስና ስጋቶች አደገኛ ተጽዕኖ ያላቸው ተብለው ከአንድ እስከ ሶስት በቅደም ተከተል የተቀመጡ ስጋቶች ናቸው፡፡

ሙስና ቢከሰት የሚያስከትለው ተጽዕኖ በደረጃ፡- በተቋማት ውስጥ በሚካሄዱ ግዥዎች ውስጥ ሙስና ቢከሰት የሚያስከትለዉ ተጽዕኖ በሶስት ደረጃ የተከፈለ ሲሆን እነሱም አነስተኛ፤ መጠነኛ እና ከባድ ተጽዕኖ በመባል እንደገና በደረጃ ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ በመሆኑም በግዥ በጀት ዝግጅት ወቅት

(ለተቋሙ የማያስፈልግ ዕቃ እንዲገዛ በጀት እንዲያዝ በማድረግ)፣ በጨረታ ሰነድ ዝግጅት ወቅት (የተወሰኑ ተወዳዳሪዎችን በተለየ ሁኔታ እንዲጋብዝ አድርጎ ማዘጋጀት) እና በጨረታ ሰነድ የፋይናንስ ግምገማ ወቅት ሙስና ቢከሰት ከባድ የሆነ ተጽዕኖ ሊኖረው እንደሚችል ተመላክቷል፡፡ በሌላ በኩል በጨረታ ሰነድ የቴክኒክ ግምገማ ወቅት ሙስና ቢከሰት መካከለኛ የሆነ ተጽዕኖ ሊኖረው እንደሚችል ተጠቅሷል፡፡ ዝርዝር የተጽዕኖ ደረጃውን በሰንጠረዥ ሸ1 ላይ ይመልከቱ፡፡

ሙስና ቢከሰት የሚያስከትለው ስጋት በደረጃ፡- በትምህርት ተቋማት ውስጥ በሚካሄዱ ግዥዎች ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስና ተጋላጭነትና ስጋት ግምገማ በሶስት ደረጃ የተከፈለ ሲሆን እነሱም አነስተኛ፣ መካከለኛና ከባድ በመባል በደረጃ ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ የግምገማ ደረጃው በሚካሄዱ ግዥዎች የሙስና ስጋት የመከሰት እድል በደረጃ እና ቢከሰት የሚያስከትለው ተጽዕኖ በደረጃ ተባዝተው የሚሰጡት ውጤት ነው፡፡ በመሆኑም በግዥ በጀት ዝግጅት ወቅት (ለተቋሙ የማያስፈልግ ዕቃ እንዲገዛ በጀት እንዲያዝ በማድረግ)፣ በጨረታ ሰነድ ዝግጅት ወቅት (የተወሰኑ ተወዳዳሪዎችን በተለየ ሁኔታ እንዲጋብዝ አድርጎ ማዘጋጀት) እና በጨረታ ሰነድ የፋይናንስ ግምገማ ወቅት ከባድ የሆነ የሙስና ስጋት ሊኖር እንደሚችል ተመላክቷል፡፡ በሌላ በኩል በጨረታ ሰነድ የቴክኒክ ግምገማ ወቅት መካከለኛ የሆነ የሙስና ስጋት ሊኖር እንደሚችል ተጠቅሷል፡፡ ዝርዝር የገምገማ ደረጃውን በሰንጠረዥ ሸ1 ላይ ይመልከቱ፡፡

ሰንጠረዥ ሸ1 ፡ በሚካሄዱ የግዥ ሂደቶች የሙስና ትጋላጭነትና ስጋት ትንተና እና የተጸዕኖ ደረጃ

ተ.ቁ	በሚካሄዱ የግዥ ሂደቶች የሙስና ትጋላጭነትና ስጋት	የሙስና ስጋት የመከሰት ዕድል ቅደም ተከተል	የመከሰት እድል በደረጃ			የሙስና ስጋት ቢከሰት ሊደርስ የሚችለውጉዳት ቅደም ተከተል	የሙስና ስጋት ቢከሰት የሚያመጣው የተጽዕኖ ደረጃ			የሙስና ስጋት (የሙስና ስጋት የመከሰት ዕድል*የተጽዕኖ ደረጃ)	የስጋቱ መንስኤ	የስጋቱ መፍትሄ
			ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ		ከባድ	መጠነኛ	አነስተኛ			
1	በግዥ በጀት ዝግጅት ወቅት (ለተቋሙ የማስፈልግ ዕቃ እንዲገዛ በጀት እንዲያዝ በማድረግ)	1ኛ	✓			1ኛ	✓			ከባድ	• የተጠናከር የቁጥጥር ስራ አለመኖር • ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት • በአቋራጭ ለመክበር • መመሪያና ደንብን አለማክበር • ግልጽነትና ተጠያቂነት ጉድለት	• መመሪያን ማክበር • ፈጻሚ አካላት በእቅድ እንዲመሩ ማድረግ • ከጠያቂው ክፍል ስለ እቃው እወቀት ያለው ሰው መመደብ
2	በጨረታ ሰነድ ዝግጅት ወቅት (የተወሰኑ ተወዳዳሪዎችን በተለየ ሁኔታ እንዲጋብዝ አድርጎ በማዘጋጀት)	2ኛ	✓			2ኛ	✓			ከባድ	• የተጠናከር የቁጥጥር ስራ አለመኖር • ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት • በአቋራጭ ለመክበር • መመሪያና ደንብን አለማክበር • ግልጽነትና ተጠያቂነት ጉድለት	• መመሪያን ማክበር • ፈጻሚ አካላት በእቅድ እንዲመሩ ማድረግ • ከጠያቂው ክፍል ስለ እቃው እወቀት ያለው ሰው መመደብ
3	በጨረታ ሰነድ የቴክኒክ ግምገማ ወቅት	3ኛ		✓		3ኛ		✓		መካከለኛ	• ግልጽነትና ተጠያቂነት ጉድለት • ግልጽነትና ተጠያቂነት ጉድለት	• ከጠያቂው ክፍል ስለ እቃው እወቀት ያለው ሰው መመደብ
4	በጨረታ ሰነድ የፋይናንስ ግምገማ ወቅት	4ኛ	✓			4ኛ	✓			ከባድ	• የተጠናከር የቁጥጥር ስራ አለመኖር • ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት • በአቋራጭ ለመክበር • መመሪያና ደንብን አለማክበር • ግልጽነትና ተጠያቂነት ጉድለት	• መመሪያን ማክበር • ፈጻሚ አካላት በእቅድ እንዲመሩ ማድረግ • ከጠያቂው ክፍል ስለ እቃው እወቀት ያለው ሰው መመደብ
5	በእቃ ወይም አገልግሎት ርክክብ ወቅት (በጨረታ ሰነዱ ስፔስፊኬሽን መሰረት ዕቃዎችን ባለመረከብ)	5ኛ			✓	5ኛ		✓		ነስተኛ		
6	ሌላ ካለ ቢዘረዝሩልን…	6ኛ			✓	6ኛ		✓		አነስተኛ		

4.4. በፈቃድ አሰጣጥና ስረዛ የስራ ሂደቶች ዉስጥ የሙስና ስጋት ምዘና

በዚህ ንዕስ ክፍል የፈቃድ አሰጣጥና ስረዛ በሚያካሂዱ የትምህርት ተቋማት ውስጥ የሙስና ስጋቶችን የመለየትና የመከሰት ዕድላቸዉን በቅደም ተከተል የማስቀመጥ ስራ፣ የመከሰት ዕድላቸዉንና ቢከሰቱ ሊያስከትሉት የሚችሉትን ተጽዕኖ በደረጃ በማስቀመጥ የሙስና ስጋት ምዘና ተካሄዷል፡፡

የፈቃድ አሰጣጥና ስረዛ የስራ ሂደቶች ዉስጥ የሙስና ስጋት ትንተና፡- የጥናቱ ተሳታፊዎች በትምህርት ተቋማት ውስጥ የፈቃድ መስጠትና ስረዛ በሚካሂዱ ተቋማት ውስጥ ያለዉን የሙስና ስጋት እንዲለዩ ብሎም የመከሰት ዕድላቸውን በቅደም ተከተል እንዲገልጹ በተጠየቁት መሰረት በትምህርት ተቋማት በሚከናወኑ የፍቃድ አሰጣጥና ስረዛ ተግባራት ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉ ሶስት የሙስና ተጋላጭነትና ስጋቶች የተለዩ ሲሆን የመከሰት ዕድልም በቅደም ተከተል ለማስቀመጥ ተሞክሯል (ሰንጠርዥ ቀ1ን ይመልከቱ)፡፡ በመሆኑም ወደ ሶስት የሚሆኑ ሊከሰቱ የሚችሉ ስጋቶች የተለዩ ሲሆን ህጉ ከሚፈቅደው ውጭ የሙያ ፈቃድ መስጠት፣ ህጉ ከሚፈቅደው ውጭ የሙያ ፈቃድ ዕድሳት ማካሄድ እና ህጉ ከሚፈቅደው ውጭ የሙያ ፈቃድ ስረዛ ማካሄድ ተብለው የተለዩ የሙስና ስጋቶች ከፍተኛ ዕድል ያላቸው ተብለው ከአንድ እስከ ሶስት በቅደም ተከተል የተቀመጡ ስጋቶች ናቸው፡፡

የሙስና ስጋቶች የመከሰት ዕድል በደረጃ፡- በትምህርት ተቋማት በሚካሄዱ የሙያ ፈቃድ አሰጣጥና ስረዛ ሂደቶች ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስና ስጋቶችን እና የመከሰት ዕድላቸው በሶስት ደረጃ የተከፈለ ሲሆን እነሱም ዝቅተኛ፤ መካከለኛ እና ከፍተኛ በመባል እንደገና በደረጃ ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ በመሆኑም ህጉ ከሚፈቅደው ውጭ የሙያ ፈቃድ ስረዛ ማካሄድ ሙስና ከፍተኛ የመከሰት ዕድል ያለው በመሆን ተጠቅሷል፡፡ በሌላ በኩል ህጉ ከሚፈቅደው ውጭ የሙያ ፈቃድ ዕድሳት ማካሄድ የሙስና ስጋት የመከሰት ዕድል መካከለኛ እንደሆነ ተመላክቷል፡፡

የሙስና ስጋት ቢከሰት የሚያስከትለው ተጽዕኖ፡- በትምህርት ተቋማት ውስጥ በሚደረጉ የሙያ ፈቃድ አሰጣጥና ስረዛ ስራዎች ውስጥ ሙስና ቢከሰት ሊያስከትል የሚችለውን ተጽዕኖ የመረጃ ትንተና የተካሄደ ሲሆን ከስጋቶቹ ውስጥ ህጉ ከሚፈቅደው ውጭ የሙያ ፈቃድ መስጠት፤ ህጉ ከሚፈቅደው ውጭ የሙያ ፈቃድ ዕድሳት ማካሄድ እና ህጉ ከሚፈቅደው ውጭ የሙያ ፈቃድ ስረዛ ማካሄድ ተብለው የተለዩ የሙስና ስጋቶች አደገኛ ተጽዕኖ ያላቸው ተብለው ከአንድ እስከ ሶስት በቅደም ተከተል የተቀመጡ ስጋቶች ናቸው፡፡

የሙስና ስጋት ቢከሰት የሚያስከትለው ተጽዕኖ በደረጃ፡- በተቋማት ውስጥ በሚካሄድ ፈቃድ አሰጣጥና ስረዛ ስራዎች ውስጥ ሙስና ቢከሰት የሚያስከትለዉ ተጽዕኖ በሶስት ደረጃ የተከፈለ ሲሆን እነሱም አነስተኛ፣ መጠነኛ እና ከባድ ተጽዕኖ በመባል እንደገና በደረጃ ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ በመሆኑም ህጉ ከሚፈቅደው ውጭ የሙያ ፈቃድ መስጠት ቢከሰት ከባድ የሆነ ተጽዕኖ ሊኖረው እንደሚችል ተመላክቷል፡፡ በሌላ በኩል ህጉ ከሚፈቅደው ውጭ የሙያ ፍቃድ ስረዛ ማካሄድ ቢከሰት አነስተኛ የሆነ ተጽዕኖ ሊኖረው እንደሚችል ተጠቅሷል፡፡ ዝርዝር የተጽዕኖ ደረጃውን በሰንጠረዥ ቀ1 ላይ ይመልከቱ፡፡

የሙስና ስጋት ቢከሰት የሚያስከትለው ስጋት በደረጃ፡- የግምገማ ደረጃው በሚካሄደው የፍቃድ አገልግሎት ላይ የሙስና ስጋት የመከሰት እድል በደረጃ እና ቢከሰት የሚያስከትለው ተጽዕኖ በደረጃ ተባዝተው የሚሰጡት ውጤት ነው፡፡ በመሆኑም ህጉ ከሚፈቅደው ውጭ የሙያ ፈቃድ መስጠት፤ ህጉ ከሚፈቅደው ውጭ የሙያ ፈቃድ ማደስ እና ህጉ ከሚፈቅደው ውጭ የሙያ ፈቃድ ስረዛ ማካሄድ መካከለኛ የሆኑ የሙስና ስጋቶች እንደሆኑ ተመላክቷል፡፡ ዝርዝር የገምገማ ደረጃውን በሰንጠረዥ ቀ1 ላይ ይመልከቱ፡፡

ሰንጠረዥ ቀ1 ፡ የፈቃድ አሰጣጥና ስረዛ የስራ ሂደቶች ዉስጥ የሙስና ተጋላጭነትና ስጋት ትንተና እና የተጸዕኖ ደረጃ

ተ.ቁ	የፈቃድ አሰጣጥና ስረዛ የስራ ሂደቶች ዉስጥ የሙስና ተጋላጭነትና ስጋት	የሙስና ስጋት የመከሰት ዕድል ቅደም ተከተል	የመከሰት እድል በደረጃ			የሙስና ስጋት ቢከሰት ሊደርስ የሚችለውጉዳት ቅደም ተከተል	የሙስና ስጋት ቢከሰት የሚያመጣው የተጽዕኖ ደረጃ			የሙስና ስጋት (የሙስና ስጋት የመከሰት ዕድል*የተጽዕኖ ደረጃ)	የስጋቱ መንስኤ	የስጋቱ መፍትሄ
			ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ		ከባድ	መጠነኛ	አነስተኛ			
1	ህጉ ከሚፈቅደዉ ዉጭ የሙያ ፍቃድ መስጠት	1st			✓	1st	✓			**መካከለኛ**	• የተጠናከረ የቁጥጥር ስርዓት አለመኖር • ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት • በአቋራጭ ለመክበር • የአመራር ልል መሆን • አመራሩ የሚጠበቅበትን ሃላፊነት አለመወጣት • የተጠያቂነት ስርዓት ውስንነት • ተቋማት የሚሰጡት የእውቅና ፍቃድ አዋጅና መመሪያን ያሟላ አለመሆን	• አጥፊዎችን አጋልጦ ለፍትህ ማቅረብና ተመጣጣን ቅጣት • ስራን በህጉ መሰረት ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማስፈን • ጠንካራ የሆነ የቁጥጥርና ክትትል ስርዓት ማስፈን
2	ህጉ ከሚፈቅደዉ ዉጭ የሙያ ፍቃድ ማደስ	2nd		✓		2nd		✓		**መካከለኛ**	• ለእውቅና እድሳት ግምገማ የሚያደርጉ ባለሙያዎች ተመሳሳይ የመገምገሚያ መስፈርት አለመጠቀም • ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት • በአቋራጭ ለመክበር • የተጠያቂነት ስርዓት ውስንነት • ተቋማት የሚሰጡት የእውቅና ፍቃድ አዋጅና መመሪያን ያሟላ አለመሆን	• አጥፊዎችን አጋልጦ ለፍትህ ማቅረብና ተመጣጣን ቅጣት • ስራን በህጉ መሰረት ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማስፈን • ጠንካራ የሆነ የቁጥጥርና ክትትል ስርዓት ማስፈን
3	ህጉ ከሚፈቅደዉ ወጭ የሙያ ስረዛ ማካሄድ	3rd	✓			3rd			✓	**መካከለኛ**	• ለእውቅና እድሳት ግምገማ የሚያደርጉ ባለሙያዎች ተመሳሳይ የመገምገሚያ መስፈርት አለመጠቀም • ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት • በአቋራጭ ለመክበር • የተጠያቂነት ስርዓት ውስንነት	• አጥፊዎችን አጋልጦ ለፍትህ ማቅረብና ተመጣጣን ቅጣት • ስራን በህጉ መሰረት ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማስፈን • ጠንካራ የሆነ የቁጥጥርና ክትትል ስርዓት ማስፈን
4	ሌላ ካለ ቢዘረዝሩልን	4th			✓	4th			✓	**አነስተኛ**		

4.5. በህንፃ ግንባታና ዕድሳት ወቅት የሚከሰቱ የሙስና ተጋላጭነትና ስጋት ትንተና እና የተጽዕኖ ደረጃ

በዚህ ንዑስ ክፍል በህንፃ ግንባታና እድሳት ወቅት የሚከሰቱ የሙስና ስጋቶችን የመለየትና የመከሰት ዕድላቸዉን በቅደም ተከተል የማስቀመጥ ስራ፣ የመከሰት ዕድላቸዉንና ቢከሰቱ ሊያስከትሉት የሚችሉትን ተጽዕኖ በደረጃ በማስቀመጥ የሙስና ስጋት ምዘና ይካሄዳል፡፡

በህንፃ ግንባታና ዕድሳት ወቅት የሚከሰት የሙስና ስጋት ትንተና፡- የጥናቱ ተሳታፊዎች በትምህርት ተቋማት ውስጥ በሚከናወኑ የህንጻ ግንባታና ዕድሳት ያለዉን የሙስና ተጋላጭነት ስጋት እንዲለዩ ብሎም የመከሰት ዕድላቸውን በቅደም ተከተል እንዲገልጹ በተጠየቁት መሰረት በትምህርት ተቋማት በሚካሄዱ የግንባታና ዕድሳት ተግባራት ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉ አምስት የሙስና ስጋቶች የተለዩ ሲሆን ስጋቶቹ የመከሰት ዕድልም በቅደም ተከተል ለማስቀመጥ ተሞክሯል (ሰንጠረዥ በ13 ይመልከቱ)፡፡ በመሆኑም ወደ አምስት የሚሆኑ ሊከሰቱ የሚችሉ ስጋቶች የተለዩ ሲሆን በግንባታ ስራዎች ቁጥጥርና ክትትል ጊዜ ጥራቱን ያልጠበቀ ግንባታ እንዲካሄድ መፍቀድ፤ በጨረታ ጊዜ ብቃት የሌለዉ ተቋራጭ ጨረታዉን እንዲያሸንፍ በማድረግ፤ ጨረታዉ ከተጠናቀቀና አሸናፊዉ ከተለየ በኂላ በግዥና በግንባታ ስራዎች ቁጥጥርና ክትትል ጊዜ ጥራቱን ያልጠበቀ የግንባታ ግባአቶች ስራ ላይ እንዲዉሉ መፍቀድ ተብለው የተለዩ የሙስና ስጋቶች ከፍተኛ ዕድል ያላቸው ተብለው ከአንድ እስከ አራት በቅደም ተከተል የተቀመጡ ስጋቶች ናቸው፡፡

የሙስና ስጋቶች የመከሰት ዕድል በደረጃ፡- በትምህርት ተቋማት በሚካሄዱ የግንባታ ስራዎች ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስና ስጋቶችን እና የመከሰት ዕድላቸው በሶስት ደረጃ የተከፈለ ሲሆን እነሱም ዝቅተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ በመባል እንደገና በደረጃ ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ በመሆኑም በግንባታ ስራዎች ቁጥጥርና ክትትል ጊዜ ጥራቱን ያልጠበቀ ግንባታ እንዲካሄድ መፍቀድ ከፍተኛ የመከሰት ዕድል ያለው የሙስና ስጋት በመሆን ተጠቅሷል፡፡ በሌላ በኩል በጨረታ ጊዜ ብቃት የሌለዉ ተቋራጭ ጨረታዉን እንዲያሸንፍ ማድረግ   የመከሰት ዕድሉ አነስተኛ እንደሆነ ተመላክቷል፡፡

የሙስና ስጋት ቢከሰት የሚያስከትለው ተጽዕኖ፡- በትምህርት ተቋማት ውስጥ በሚደረጉ የግንባታ ስራዎች መካከል ሙስና ቢከሰት ሊያስከትል የሚችለውን ተጽዕኖ የመረጃ ትንተና የተካሄደ ሲሆን ከስጋቶቹ ውስጥ በግንባታ ስራዎች ቁጥጥርና ክትትል ጊዜ ጥራቱን ያልጠበቀ ግንባታ እንዲካሄድ መፍቀድ፤በጨርታ ጊዜ ብቃት የሌለዉ ተቋራጭ ጨረታዉን እንዲያሸንፍ በማድረግ፤በህንፃ ርክክብ ጊዜ ጥራቱ የተጓደለ ህንፃ መረከብ እና የተሳሳተ የህንጻ ዲዛይን በማውጣት ተብለው የተለዩ የሙስና ስጋቶች አደገኛ ተጽዕኖ ያላቸው ተብለው ከአንድ እስከ አራት በቅደም ተከተል የተቀመጡ ስጋቶች ናቸው፡፡

የሙስና ስጋት ቢከሰት የሚያስከትለው ተጽዕኖ በደረጃ፡- በተቋማት ውስጥ በሚካሄዱ ግንባታዎች ሙስና ቢከሰት የሚያስከትለዉ ተጽዕኖ በሶስት ደረጃ የተከፈለ ሲሆን እነሱም አነስተኛ፣ መጠነኛ እና ከባድ ተጽዕኖ በመባል እንደገና በደረጃ ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ በመሆኑም በግንባታ ስራዎች ቁጥጥርና ክትትል ጊዜ ጥራቱን ያልጠበቀ ግንባታ እንዲካሄድ መፍቀድ ቢከሰት ከባድ የሆነ ተጽዕኖ ሊኖረው እንደሚችል ተመላክቷል፡፡ በሌላ በኩል በጨረታ ጊዜ ብቃት የሌለዉ ተቋራጭ ጨረታዉን እንዲያሸንፍ በማድረግ እና የተሳሳት የህንጻ ዲዛይን በማውጣት ቢከሰቱ አነስተኛ የሆነ ተጽዕኖ ሊኖራቸው እንደሚችል ተጠቅሷል፡፡ ዝርዝር የተጽዕኖ ደረጃውን በሰንጠረዥ በ1 ላይ ይመልከቱ፡፡

የሙስና ስጋት ቢከሰት የሚያስከትለው ስጋት በደረጃ፡- በትምህርት ተቋማት ውስጥ ከሚከናወኑ የግንባታ ስራዎች መካከል ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስና ስጋት ግምገማ በሶስት ደረጃ የተከፈለ ሲሆን እነሱም አነስተኛ፣ መካከለኛና ከባድ በመባል በደረጃ ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ የግምገማ ደረጃው በሚካሄዱ የህንፃ ግንባታ ስራዎች ላይ የሙስና ስጋት የመከሰት እድል በደረጃ እና ቢከሰት የሚያስከትለው ተጽዕኖ በደረጃ ተባዝተው የሚሰጡት ውጤት ነው፡፡ በመሆኑም በግንባታ ስራዎች ቁጥጥርና ክትትል ጊዜ ጥራቱን ያልጠበቀ ግንባታ እንዲካሄድ መፍቀድ እና በህንፃ ርክክብ ጊዜ ጥራቱ የተጓደለ ህንፃ መረከብ ከፍተኛ የሆኑ የሙስና ስጋቶች እንደሆኑ ተመላክቷል፡፡ ዝርዝር የገምገማ ደረጃውን በሰንጠረዥ በ1 ላይ ይመልከቱ፡፡

ሰንጠረዥ በ1 ፡ ለሙስና እና ለብልሹ አሰራር ሊጋለጡ የሚችሉ የስራ ሂደቶች ትንተና እና የተጸዕኖ ደረጃ

ተ.ቁ	ለሙስና እና ለብልሹ አሰራር ሊጋለጡ የሚችሉ የስራ ሂደቶች	የሙስና ስጋት የመከሰት ዕድል ቅደም ተከተል	የመከሰት እድል በደረጃ			የሙስና ስጋት ቢከሰት ሊደርስ የሚችለውጉዳት ቅደም ተከተል	የሙስና ስጋት ቢከሰት የሚያመጣው የተጽዕኖ ደረጃ			(የሙስና ስጋት የመከሰት ዕድል*የተጽዕኖ ደረጃ)	የስጋቱ መንስኤ	የስጋቱ መፍትሄ
			ከፍተኛ	መካከለኛ	ዝቅተኛ		ከባድ	መጠነኛ	አነስተኛ			
1	በጨርታ ጊዜ ብቃት የሌለዉ ተቋራጭ ጨረታዉና እንዲያሸንፍ በማድረግ	2nd			✓	2nd			✓	አነስተኛ		
2	በግንባታ ስራዎች ቁጥጥርና ክትትል ጊዜ ጥራቱን ያልጠበቀ ግንባታ እንዲካሄድ መፍቀድ	1st	✓			1st	✓			ከባድ	• የተጠናከረ የቁጥጥር ስርዓት አለመኖር • ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት • በአቋራጭ ለመክበር • ተጠያቂነትና ግልጽነት የጎደለው አሰራር መኖር • ሰራተኞች በብቃታቸውና በችሎታቸው ተመዝነው አለመቀጠር	• አጥፊዎችን አጋልጦ ለፍትህ ማቅረብና ተመጣጣን ቅጣት • ስራን በህጉ መሰረት ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማስፈን • ጠንካራ የሆነ የቁጥጥርና ክትትል ስርዓት ማስፈን
3	በገንባታ ስራዎች ቁጥጥርና ክትትል ጊዜ ጥራቱን ያልጠበቀ የገንባታ ግባአቶች ስራ ላይ እንዲዉሉ መፍቀድ	4th		✓		5th		✓		መካከለኛ	• የተጠናከረ የቁጥጥር ስርዓት አለመኖር • ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት • በአቋራጭ ለመክበር • ተጠያቂነትና ግልጽነት የጎደለው አሰራር መኖር • ሰራተኞች በብቃታቸውና በችሎታቸው ተመዝነው አለመቀጠር	• አጥፊዎችን አጋልጦ ለፍትህ ማቅረብና ተመጣጣን ቅጣት • ስራን በህጉ መሰረት ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማስፈን • ጠንካራ የሆነ የቁጥጥርና ክትትል ስርዓት ማስፈን
4	በህንፃ ርክክብ ጊዜ ጥራቱ የተጓደለ ህንፃ መረከብ	5th		✓		3rd		✓		ከባድ	• ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት • በአቋራጭ ለመክበር • ተጠያቂነትና ግልጽነት የጎደለው አሰራር መኖር • የህግ መላላት	• አጥፊዎችን አጋልጦ ለፍትህ ማቅረብና ተመጣጣን ቅጣት • ጠንካራ የሆነ የቁጥጥርና ክትትል ስርዓት ማስፈን
5	የተሳሳት የህንጻ ዲዛይን በማውጣት	3rd		✓		4th			✓	አነስተኛ		
6	ሌላ ካለ ቢዘረዝሩልን…	6th			✓	6th			✓	አነስተኛ		

ክፍል 5፡ ማጠቃለያና ምክረ-ሃሳብ

ማጠቃለያ

የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው በትምህርት ሴክተር ውስጥ በሚገኙ የትምህርት ተቋማት ውስጥ የተለያዩ የሙስና ስጋት አይነቶች ይታያሉ። የሙስና አይነቶች የተለያዩ የመሆናቸውን ያህል ተቋማቱ ሙስናን ለመከላከልም ሆነ ከተከሰተ በኋላ ለማረም ያላቸው የአመራር ሁኔታና የዘረጉት አሰራር የተለያየ ነው። የሴክተሩ ዝርዝር የሙስና ስጋቶችና ለስጋቶቹ መከሰት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ሶስት ዋና ዋና ጉዳዮች ማለትም የግለሰቦች የሞራል አቋም መውደቅ፣ ሙስናን ለመከላከል የሚያስችል አሰራር አለመኖርና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ተዳሰዋል። ከዚህ ጋሬ በተያያዘ የተቋማት ቁመና በዝርዝር በሰነዱ ክፍል ሶስት ውስጥ ቀርቧል።

በሰነዱ ክፍል አራት በቀረበው መሰረት በተለያዩ የትንተና ዘዴዎች ተለይተው የወጡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ከሆነ ከአንድ እስከ አስራ ዘጠኝ ድረስ በቅደም ተከተል ሊቀመጡ የሚችሉ የሙስና አይነቶች ሲኖሩ ከእነዚህም መካከል ቀዳሚዎቹ አራቱ የሚከተሉት ናቸው፡- (1) የመምህራን በተደጋጋሚ ክፍል አለመግባት፣ (2) ህገወጥ ቅጥር፣ ዝዉዉር ና ደረጃ ዕድገት፣ (3) የአሰራር ግልጥነት መጓደል፣ እና (4) ግዥዎች ህግና ደንብን ተከትለዉ አለመከናዎን ናቸው። በዝርዝር ከተለዩ የሙስና አይነቶች መካከል ሁሉም ተመሳሳይ ጉዳት ያደርሳሉ ተብሎ ስለማይታሰብ ሁሉንም በደረጃ ለማስቀመጥ ተሞክሯል። ከዚህ አንፃር ቢከሰቱ የበለጠ ጉዳት ሊያደርሱ ከሚችሉ የሙስና አይነቶች መካከል ቀዳሚዎቹ አራቱ፡- (1) የመምህራን በተደጋጋሚ ክፍል አለመግባት፣ (2) ህገወጥ ቅጥር፣ ዝዉዉርና የደረጃ ዕድገት፣ (3) በአመራሩ የሚከናወን ስርቆት፣ እና (4) ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ መስጠት ናቸው።

የመከሰት እድልን ከሚያደርሰው ተፅዕኖ ጋር በማዛመድ በተሰራው የሙስና የስጋት ደረጃ ሁሉም የሙስና አይነቶች በሶስት ደረጃ ማለትም አነስተኛ፣ መካከለኛና ከባድ በሚል ተከፋፍለዋል። ከባድ በሚል የተለዩ የሙስና አይነቶች ልዩ ትኩረት የሚፈልጉና ሁሉም የትምህርት ተቋማት ቅድሚያ ሰጥተው መፍትሄ ሊፈልጉላቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው። ከባድ በሚል የተለዩ የሙስና አይነቶች የመምህራን በተደጋጋሚ ክፍል አለመግባት፣ ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ መስጠት፣ በአመራሩ የሚከናወን ስርቆት፣ ህገወጥ ቅጥር፣ ዝዉዉር ና ደረጃ ዕድገት፣ ግዥዎች ህግና ደንብን ተከትለዉ አለመከናዎን፣ የመረጃና ማስረጃ ማጭበርበር፣ እና የአሰራር ግልጥነት መጓደል ናቸው።

የስጋት ትንተናና ምዘና ስራው የበለጠ የችግሩን ይዘት ማሳየት ይችል ዘንድ በተመረጡ የስራ ዘርፎች ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ስጋቶች ተለይተው የስጋት ምዘና ተከናውኗል፡፡ ከእነዚህ መካከል ለሙስና ተጋላጭ ተደርገው በሚወሰዱ ስምንት የስራ ክፍሎችን በመለየት የትኛው ክፍል ልዩ ትኩረት እንደሚፈልግ በተደረገው ልየታ ግዥ ክፍል፣ በሰው ሃብት ልማት አስተዳደርና ሬጂስትራር ተለይተው ወጥተዋል፡፡ በመቀጠል በግዥ ክፍል ውስጥ ከሚከናዎኑ ተግባራት መካከል በየትኛው የበለጠ የሙስና ስጋት እንደሚታይ በተደረገው ጥረት ስጋቶቹ ጎልተው የሚታዩት በግዥ ስግጅት ወቅት፣ በግዥ ሰነድ ዝግጅትና የጨረታ ሰነድ ግምገማ ወቅት መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በፈቃድ አሰጣጥ ላይ የሚታዩ ችገሮችን በተመለከተ በተደረገው ትንተና ከባድ ስጋት አለመኖሩን ለማየት ተችሏል፡፡ በመጨረሻም በህንፃ ግንባታና ዕድሳት ወቅት ሊከሰቱ ከሚችሉ ስጋቶች መካከል በግንባታ ስራዎች ቁጥጥርና ክትትል ጊዜ ጥራቱን ያልጠበቀ ገንባታ እንዲካሄድ መፍቀድና በህንፃ ርክክብ ጊዜ ጥራቱ የተጓደለ ህንፃ መረከብ እንደ ከባድ የሙስና ስጋት ተወስደዋል፡፡

ምክረ-ሃሳብ

የሙስና ስጋቶችን በደረጃ የማስቀመጥ ፋይዳው ለመፍትሄ ቅድሚያ ሰጥቶ ርምጃ ለመውሰድ እንዲረዳ ነው፡፡ ሁሉንም የሙስና አይነቶች በተመሳሳይ ጊዜ መፍትሄ ለመስጠት የጊዜ፣ የገንዘብና አቅም ውስንነት ሊኖር ስለሚችል በዚህ ጥናት ከባድ ደረጃ ላይ ናቸው ተብለው ለተለዩት የሙስና አይነቶች ቅድሚያ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንፃር የሚከተሉት ምክረ-ሃሳቦች ተለይተዋል፡፡

- በሴክተሩ የሚገኙ ተቋማት በርካታ ከመሆናቸው የተነሳ ከባድ ተብለው ከተለዩ የሙስና አይነቶች መካከል እያንዳንዱ ተቋም የሚመለከተውን የሙስና ስጋት አይነት ለይቶ መውሰድ
- ተለይተው የወጡ ስጋቶችን መነሻ በማድረግ የመፍትሄ ስትራቴጂ በማዘጋጀት አመራሩ ቀዳሚውን ተነሳሽነት በመውሰድ ስትራቴጂውን ለመተግበር መንቀሳቀስ
- ስትራቴጂ ሲነደፍም ሆነ ወደ ተግባር ሲኬድ በተቻለ መጠን ቴክኖሎጅን ለመጠቀምና ዘላቂ አሰራር መዘርጋት ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ሙስናን የመከላከል ስራ የአንድ ወቅት ስራ ሳይሆን ዘላቂነት ሊኖረው ይገባል፡፡
- ሁሉም የሴክተሩ ተቋማት ይህንን ጥናት መነሻ በማድረግ የራሳቸውን የስጋት ትንተና በየጊዜው ቢያደርጉ ሙስናን ለመከላከል አቅም የሚያገኙ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል በሁሉም ተቋማት የተገኙ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ለሙስና መከሰት እንደምክንያትነት የሚጠቀሱ የግለሰብ የሞራል አቋም፣ የአሰራር ጉዳይና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች በራሳቸው መፍትሄ ይፈልጋሉ። እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ ይቻል ዘንድ ከችግሮቹ ጋር ተመጣጣኝ የመፍትሄ ርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል። ከግለሰቦች የሞራል አቋም ጋር በተያያዘ ሰፊ የሆነ የግንዛቤ መፍጠሪያ ስራዎች ያስፈልጋሉ። ግንዛቤ ለመፍጠር ምናልባት የተለመደው አይነት ስልጠና መስጠት ብቻውን በቂ ላይሆን ይችላል። ከዚያ ይልቅ በሞራል ልእልና ስኬት ላይ የደረሱ ግለሰቦችን ታሪክ በማሳያነት ማቅረብ ወይም ይግለሰብ ህይወት የሚመዘነው ሰዎች በሚያካብቱቴ ገንዘብ ብቻ አለመሆኑን ማስረዳት። ስኬት ሲባል በብዙ መልኩ ሊታይ እንደሚችልና ሰዎች ሌሎች ሰዎችን በማገልገላቸው ወይም ለሙያቸው ታማኝ በመሆናቸው ሌላኛውን የስኬት መንገድ ሊከተሉ እነደሚችሉ ማሳየት የሚያስችሉ የግንዛቤ መፍጠሪያ መንገዶችን መከተል ያስፈልጋል። በሌላ መልኩ ደግሞ ሰዎች ከሌላ ሰው ውድቀት ሊማሩ ስለሚችሉ ሰዎች ስነምግባራዊ መንገድን ባለመከተላቸው የደረሰባቸውን ችግርም ማሳይት ይቻላል። ሙስናን ለመከላከል የሚያስችል አሰራር ካለመኖር ጋር የሚፈጠሩ ችግሮችን በተመለከተ ሊነሳ የሚችለው የመፍትሄ ሃሳብ አሰራር መዘርጋትና የተዘረጋውን አሰራር መተግበር ይሆናል። በጥናቱ ውስጥ እንደተመላከተው የአሰራር ጉዳይ ከአመራር ጋር የሚገናኝበት መስመር ስላለው አሰራር የመዘርጋትና አሰራሩን ባግባቡ የመተግበር ጉዳይ የአመራር ቁርጠኝነት ከመፍጠር ጋር ሊተሳሰር ይገባል። በመጨረሻም የኢኮኖሚ ጉዳዮችን በተመለከተ የመንግስት ሰራተኞች ገቢ ሊሻሻል የሚችልበት ሁኔታ እንዲመጣ አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል።

ከላይ የቀረቡትን የመፍትሄ ሃሳቦች ከመተግበር አንጻር የተለያዩ ተቋማት የተለያየ ሃላፊነት እንዳላቸው ማስታወስ ያስፈልጋል። በመጀመሪያ ደረጃ ሁሉም የትምህርት ተቋማት የራሳቸውን የሙስና ስጋት ከመለየትና በተቋማቸው የስልጣን ወሰን ልክ መፍትሄ ለመውሰድ ሊንቀሳቀሱ ያስፈልጋል። ከዚህ በመቀጠል የፌዴራል የስነምግባርና የፀረሙስና ኮሚሽን በበኩል ተቋማት የሙስና ስጋትን ለመቀነስ በሚያደርጉት ጥረት የሙያ ድጋፍ በማድረግና የተለያዩ የግንዛቤ መፍጠሪያ ስልቶችን በመንደፍ ሚናውን ሊወጣ ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ ኮሚሽኑ ከሌሎች የመንግስት ሃላፊዎች ጋር በመነጋገር ለሙስና መከሰት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ችግሮች የሚቀረፉበትን ሁኔታ ማፈላለግ ይጠበቅበታል።

ማጣቀሻዎች

1. Annual-Year የኦዲት ሪፖርት (2013). Ministry-of-Education.
2. Annual-Year የኦዲት ሪፖርት (2012 E-C). Ministry-of-Education
3. ዋና የኦዲት ሪፖርት (2013). በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የምርምር በጀት አስተዳደር
4. በዋና ኦዲተር (2012). በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ላይ በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዱት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች
5. በኮሚሽኑ የተዘጋጀ ተቋማዊ የሙስና መከላከል ስትራቴጂ ሰነድ
6. World Bank (2012). Diagnosing Corruption in Ethiopia: Perceptions, Realities, and the Way Forward for Key Sectors, Janelle Plummer(Ed.)
7. European Commission (2013). Study on Corruption in the Healthcare Sector/Luxembourg: Publications Office of the European Union.
8. FEACC, (2012). Ethiopia Second Corruption Perception Survey Prepared by: Kilimanjaro International Corporation Limited
9. Informal payments in the health sector: a case study from Turkey. Department of Health Care Management, Hacettepe University, Ankara, Turkey.
10. Managing conflict of interest in the public service (2003). OECD Guidelines and country experiences.
11. Regulatory mechanisms for absenteeism in the health sector: a systematic review of strategies and their implementation (2016). Journal of Healthcare Leadership.
12. H.J.P.M. (2002). Ethics and corruption in education. Results from the Expert Workshop held at the IIEP. Paris (No. 15). IIEP Observation programme policy Forum.IIEP-UNESCO

አባሪ

ሰንጠረዥ መ1: ሙስናን ለመከላከል የሚረዱ አሰራሮችና መመሪያዎችን በተመለከተ የጥናቱ ተሳታፊዎች የሰጡት ምላሽ በመቶኛ

ተ.ቁ	አሰራሮችና መመሪያዎች	የመላሾች ስርጭት በመቶኛ			
		አዎ	በሂደት ላይ	የለም	አላውቅም
1	የሥነምግባር መከታተያ ክፍል በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 መሰረትተቋቁሟል	59.6	5.9	5.9	28.5
2	የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ሥራ በተቋሙ ስትራቴጂክ ዕቅድ ዉስጥተካቷል	61.4	11.1	6.9	20.6
3	ተቋሙ በሥነምግባር የታነፀ አመራር ግንባታ አሠራር ሥርዓት አለዉ	48.6	23	15	13.3
4	ተቋሙ በሥነምግባር የታነፀ ሰራተኛ ግንባታ አሠራር ሥርዓት አለዉ	50.9	23.9	14.4	10.8
5	ለተቋሙ አመራሮችና ሠራተኞች ጥራትና ተገቢነት ያለዉ የሥነምግባር አቅምና ብቃት ማጎልበቻ ሥልጠና፤መደበኛ አሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ ይሰጣል	34.4	23.1	28.8	13.6
6	ተቋሙ የአመራርና የሰራተኞች የሥነምግባር መመሪያ አለዉ	64.6	9	10.6	15.7
7	ተቋሙ የዕቅድና የፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሪፖርት ለሕዝብና ለመንግሥት ባለድርሻ አካላት እዉነተኛ መረጃ ላይ ተመስርቶ ያቀርባል	51.7	16.2	14.8	17.3
8	ተቋሙ ስለአገልግሎቱ ጥራት፤ ተገቢነት፤ ተደራሽነትና ፍትሐዊነት ግንዛቤ ለማሳደግ የደንበኛ እና የባለድርሻ አካላት እርካታ በየወቅቱ ይለካል	37.7	26.6	21.1	14.6
9	የተቋሙ ሠራተኞች ተገልጋዩን ለማስተናገድ ቅንነትና ተዓማኒነት እንዲሁም ከብልሹ ተግባራት የጸዱ ስለመሆናቸዉ የሚያረጋግጥ አሠራር ሥርዓት አለ	48.1	21	19.9	10.8
10	በተቋሙ በመልካም ሥነምግባር አርአያ የሆኑ አመራሮችንና ሠራተኞችን የመለየትና ዕውቅና የመስጠት አሠራር ሥርዓት አለ፡፡	27	25.2	37.1	10.6
11	የተቋሙ አመራርና ሰራተኛ የመንግሥት የሥራ ሰዓት ዉጤታማ አድርጎ የመጠቀም ምጣኔ ለመከታተል አሠራር ሥርዓት ተዘርግቷል	55.3	21.5	16.1	7.2
12	በተቋሙ ሙስናና ብልሹ አሠራሮች ሲከሰቱ ጥቆማዎችን ለመቀበልና ተገቢዉን የእርምት እርምጃ ለመዉሰድ የተዘረጋ አሠራር ሥርዓት አለው	47.8	2.8	18.4	13.1
13	ተቋሙ በዉስጥና በዉጭ ኦዲተሮች የተለዩትን ግኝቶች በብልሹ አሠራርና ሙስና ምክንያት የባከኑ አለመሆናቸዉን አረጋግጧል	49.6	15.7	13.1	21.6
14	ተቋሙ የኦዲት ግኝቶችን የማረጋገጥና ተገቢዉን የማሻሻያ እርምጃ አሠራር ሥርዓት ዘርግቷል	43.8	19.9	14.7	21.6

ሰንጠረዥ መ2: በተቋማት የመረጃ ግልጽነት ደረጃ በተመለከተ የጥናቱ ተሳታፊዎች የሰጡት መልስ

ተ.ቁ	የመረጃ ግልጽነት	የመላሾች ስርጭት በመቶኛ			
		እስማማለሁ	በመጠኑ እስማማለሁ	አልስማማም	አላውቅም
1	የተቋሙ ፖሊሲና ስትራቴጂክ ዕቅድ የመረጃ ግልጽነት አለው	53.6	29.7	9.2	7.5
2	የተቋሙ ህግና መመሪያዎች የመረጃ ግልጽነት አለው	51.2	30.5%	12.3	5.8
3	የመንግሥት ዓመታዊ መደበኛና ካፒታል በጀት አጠቃቀም የመረጃ ግልጽነት	41	25.4	18	15.6
4	የፕሮጀክቶች አስተዳደር የመረጃ ግልጽነት አላቸው	27.7	24.5	22.7	25.1
5	ፕሮጀክቶች የበጀት መረጃ ግልጽነት አላቸው	30.5	25.4	20.9	23
6	ወቅታዊና ዓመታዊ የተቋሙ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት የመረጃ ግልጽነት	50.6	27.4	13.3	8.7
7	ወቅታዊና ዓመታዊ የተቋሙ የበጀት አፈጻጸም ሪፖርት የመረጃ ግልጽነት	42.1	28.8	16.9	12.1
8	ወቅታዊና ዓመታዊ የተቋሙ ግዥ አፈጻጸም ሪፖርት የመረጃ ግልጽነት	28	28.3	26.1	17.7
9	ዓመታዊ የተቋሙን ንብረት ቆጠራ የሚያሳየው ሪፖርት የመረጃ ግልጽነት	35.7	28.2	20.4	15.8
10	ተቋሙ የሚያስወግደዉ ንብረት የመረጃ ግልጽነት አለው	28.9	24	23.3	23.8
11	በገለልተኛ አካል የተመዘነ ዓመታዊ የደንበኛ እርካታ ሪፖርት ግልጽነት	16.7	22.3	28.8	32.3

ሰንጠረዥ መ3: የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አቅምና ብቃት ስለማሳደግና ማጎልበ

ተ.ቁ	የሥነምግባር አቅምና ብቃት ማጎልበ	እስማማለሁ	በመጠኑ እስማማለሁ	አልስማማም	አላውቅም
1	የተቋሙ የበላይ አመራር የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ምክረ-ሐሳቦችን መነሻ በማድረግ ተቋማዊ አሠራር ሥርዓት ግልጽነትን አሻሽሏል	24.2	34.6	20.5	20.7
2	የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ተልዕኮ ለማስተባበር አቅምና ብቃት አለዉ	35.8	30	19.3	14.8
3	የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ የመምራት አቅምና ብቃት አለዉ/አላት	35.2	29.4	17.1	18.3
4	የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ባለሙያዎች ተልዕኳቸዉን ለማከናወን በቂ አቅምና	29.6	35.6	16.4	18.5

	ብቃትአላቸዉ				
5	የተቋሙ ሥነምግባር መከታተያ ክፍል ከተቋሙ ሥራ ክፍሎች ጋር ትስስር፤ ትብብርና ቅንጅት በመፍጠር የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ተልዕኮ ይወጣል	30	32.6	20.3	17
6	የሥነምግባር መከታተያ ክፍል በተቋሙ ሙስና እንዲቀንስና ሥነምግባር ጉድለት እንዲታረም አሠራር ሥርዓት፤አቅምና ብቃት አጎልብቷል	24.9	35.1	25.2	14.7

ሰንጠረዥ መ4. የጥናቱ ተሳታፊዎች ስለትምህርት ተቋማት የሙስና ሥጋት የመቀነስና የግልጽነት ዕድገት ደረጃ በተመለከተ የሰጡት መልስ

ተ.ቁ	የግልጽነት ዕድገት ደረጃ	የመላሾች ስርጭት በመቶኛ			
		እስማማለሁ	በመጠኑ እስማማለሁ	አልስማማም	አላውቅም
1	የአመራርና የሰራተኞችን የሥነምግባር ጉድለት ለመቆጣጠርና ለማረም የተቋሙ አመራር በቂ ግንዛቤና ተነሳሽነት አለዉ	37.3	33.9	20.1	8.8
2	የተቋሙ ፖሊሲ፤ ስትራቴጂ፤ ዕቅዶችንና ፕሮጀክቶችን ከሰነድነት ወደተግባር የመቀየር አቅምና ብቃት አለዉ	35	40.3	16.7	8
3	የተቋሙ ሁሉም አመራሮችና ሰራተኞች በተልዕኮና ርዕይ የጋራ ግንዛቤ አላቸዉ	30.6	39.3	21.5	8.6
4	በተቋሙ ያሉ ባለሙያዎች የሥራና የሙያ ሥነምግባር ያከብራሉ	41.3	41	13.3	4.5
5	በተቋሙ ያታዊ ትንኮሳዎችና ብልሹ ሥነ ምግባር ተጋላጭነት ለመከላከል የተዘረጋ እናየጎለበተ የ አሠራር ሥርዓት አለ	37.5	28.8	16.1	17.6
6	የተቋሙ የበላይ አመራር የሥነምግባር ልህቀት ሙስናን የመከላከል አቅምና ብቃት አለው	40.1	29.9	19.4	10.5
7	የተቋሙ የመካከለኛ አመራሮች የሥነምግባር ልህቀት ሙስናን የመከላከል አቅምና ብቃት አላቸው	31	37.5	20.7	10.8
8	የተቋሙ የመጀመሪያ ደረጃ አመራሮች የሥነምግባር ልህቀት ሙስናን የመከላከል አቅምና ብቃት አላቸው	29.3	36.5	21.3	12.7
9	የተቋሙ ሰራተኞች የሥነምግባር ልህቀት ሙስናን የመከላከል አቅምና ብቃት አላቸው	29.5	40.3	18.8	11.2
10	የአመራሩና የሰራተኛዉ የብልሹ ተግባራት መገምገመያ ስርዓት ተዘርግቷል	24.6	35	22.4	17.7
11	በተቋሙ አገልግሎት የደንበኛና የባለድርሻ ቅሬታና አቤቱታ ማቅረቢያ ስርዓት ተዘርግቷ	40.6	29.5	17	12.8
12	በተቋሙ የአመራሩና የሰራተኛዉ የብልሹ ተግባራት መገምገመያ ስርዓት ተዘርግቷል	30	25.4	26	18.4

ሰንጠረዥ መ5. የተቋማት የሙስና እና ብልሹ ተግባራትን መረጃ የማመንጨት አቅመና ብቃትን የተሳታፊዎችን እይታ የሚገልጽ ሰንጠረዥ

ተ.ቁ	መረጃ የማመንጨት አቅመና ብቃት	እስማማለሁ	በመጠኑ እስማማለሁ	አልስማማም	አላውቅም
1	የተቋሙ የበላይ አመራር ጥቆማዎችን የ መቀበልና ውሳኔ የመስጠት ዝግጁነት፤ተነሳሽነትና ተግባራዊ የማድረግ አቅም አለው	40.2	31.7	20.4	7.5
2	ተቋሙ የሙስናና ብልሹ ተግባራት ጥቆማዎችን በማደራጀት ለኮሚሽኑ የማቅረብ አቅም እና ብቃት አለው፡፡	29.8	30.3	22.3	17.6
3	ተቋሙ የሙስናና ብልሹ ተግባራት ጥቆማዎችን እና ምክረ ሃሳቦችን ወስዶ ተግባራዊ አድርጓል፡፡	32.5	32.1	22.9	12.4
4	ተቋሙ የተመዘበረ ሀብት በመረጃ ላይ በመመስረትና ክትትል በማድረግ ለማስመለስ ጥረት አድርጓል፡፡	33	28	21.6	17.3
5	ተቋሙ ጠቋሚዎች የሙስናና ብልሹ ተግባራት ጥቆማ እንዲያቀርቡ የማበረታትና የማነሳሳት ስራ ይሰራል፡፡	26.8	31.9	23.7	17.5
6	ተቋሙ ተገልጋይ እና ባለድርሻ አካላት ጥቆማ እንዲያቀርቡ ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ሰርቷል፡፡	24.9	30.8	26.8	17.3
7	ተቋሙ ጠቋሚዎችን የሥራና የህይወት ዋስትና ከላለ/ጥበቃ እንዲሰጣቸው ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል ፡፡	12.3	24.2	31.4	32
8	በተቋሙ ተጨባጭ ሁኔታ ሙስናና ብልሹ አሠራር ለመከላከል የሚያግዙ ልዩ ልዩ አደረጃጀቶችን፡ክበቦችንና ንቅናቄዎችን እንዲፈጠሩ ያበረታታል፡፡	22.9	29.3	30.4	17.2
9	ተቋሙ ዓመታዊ ዕቅድና በጀት አፈጻጸም ሪፖርት ለሕዝብ ተደራሽ አድርጓል ፡፡	37.4	27.7	20.1	14.5

10	ከሙስና እና ብልሹ ተግባር የጸዱ ስለመሆናቸዉ ጥቆማ የመቀበል የሕዝብና የባለድርሻ አካላት አስተያየት የመሰብሰብ ስርዓት አለው፡፡	25.3	30.3	26.5	17.8
11	ተቋሙ ሙስና እና ብልሹ ተግባር የመተንተንና ማሻሻያ እርምጃዎችን የመዉሰድ አሠራር ሥርዓት ዘርግቷል፡፡	20	31.8	27.2	21
12	ሙስና እና ብልሹ ተግባራት መረጃ ጥቆማ አቅርቦትና የጠቋሚዎች የማበረታቻ አሠራር ሥርዓትና ተግባር አለው፡፡	14.1	22.7	33.9	29.1
13	የሙስና ተግባራት መረጃና ማስረጃ፤ አቅርቦትና የፍትህ ዉሳኔ አሠጣጥ ሰርዓት አለው፡፡	20.1	26.8	25.9	27.1
14	በተቋሙ የሙስና መረጃ ጥቆማ በቴክኖሎጂ አማራጮች የማከናወን ዝንባሌ፡፡	11.7	23	35.8	29.4
15	የሀብት ምዝገባና ማሳወቅ አዋጅ አለማክበር የሚያስከትለዉ ቅጣት ግንዛቤ ደረጃ፡፡	44.4	23	16.7	15.8
16	የሀብት ምዝገባና ማሳወቅ አዋጅ ለጠቋሚዎች የሚያስገኘዉ ጥቅም ግንዛቤ፡፡	36.2	23.5	20	20.3

አባሪ ሀ፡ የመጠይቅ ናሙና መጠን እና የተቋማትን ዝርዝር የያዘ መረጃ

ዘርፍ	ሴክተር	ተ ቁ	ተቋም	ተቋሙ የሚገኝበት ቦታ	የመጠይቅ ብዛት	ምርመራ
ማህበራዊ	ትምህርት	1	ትምህርት ሚኒስቴር	አዲስ አበባ	63	
		2	የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት	አዲስ አበባ	79	
		3	ትምህርትና ስልጠና ስልጣን	አዲስ አበባ	24	
		4	አዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቢሮ	አዲስ አበባ	24	
		5	ቦሌ ክ/ከ ትምህርት መምሪያ	አዲስ አበባ	14	
		6	ን/ላፍቶ ክ/ክ ትመርት መምሪያ	አዲስ አበባ	15	
		7	አዲስ አበባ ከተማ ቴ/ሙ/ ትምህርት ስልጠና ቢሮ	አዲስ አበባ	24	
		8	አራዳ ቴ/ሙ/ስ መምሪያ	አዲስ አበባ	5	
		9	ቦሌ ቴ/ሙ/ስ መምሪያ	አዲስ አበባ	5	
		10	አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ	አዲስ አበባ	25	
		11	ዩኒቲ ዩኒቨርስቲ (አ አ)	አዲስ አበባ	45	
		12	ኮተቤ መምህራን ኮሌጅ	አዲስ አበባ	16	
		13	ጌጅ ኮሌጅ (አ አ)	አዲስ አበባ	15	
		14	ጀኔራል ዉንጌት ቴ/ሙ/ ኮሌጅ	አዲስ አበባ	15	
		15	አራዳ የመንግስት 1ኛ ደ/ት/ቤት	አዲስ አበባ	4	
		16	ን/ላ/ የመንግስት 1ኛ ደ/ት/ቤት	አዲስ አበባ	4	
		17	ቦሌ የግል 1ኛ ደ/ት/ቤት	አዲስ አበባ	4	
		18	ን/ላ/ የግል 1ኛ ደ/ት/ቤት	አድስ አበባ	8	
		19	አራዳ የመንግስት 2ኛ ደ/ት/ቤት	አዲስ አበባ	4	
		20	ቦሌ የመንግስት 2ኛ ደ/ት/ቤት	አዲስ አበባ	4	
		21	ን/ላ/ የመንግስት 2ኛ ደ/ት/ቤት	አዲስ አበባ	4	
		22	አራዳ የግል 2ኛ ደ/ት/ቤት	አዲስ አበባ	8	
		23	ቦሌ የግል 2ኛ ደ/ት/ቤት	አዲስ አበባ	4	
		24	ኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ	አዲስ አበባ	24	
		25	ጅማ ዞን ትምህርት መምሪያ	ጅማ	10	
		26	ምዕራብ አርሲ ትምህርት መምሪያ	ሻሸመኔ	10	
		27	ምስራቅ ሸዋ ትምህርት መምሪያ	አዳማ	10	
		28	ኦሮሚያ ቴ/ሙ/ት/ስ ቢሮ	አዲስ አበባ	13	
		29	ጅማ ዞን ቴ/ሙ/ት/ስ መምሪያ	ጅማ	5	
		30	ምዕራብ አርሲ ቴ/ሙ/ት/ስ መምሪያ	ሻሸመኔ	5	
		31	ምስራቅ ሸዋ መምሪያ	አዳማ	5	
		32	አርሲ ዩኒሸርስቲ	አሰላ	45	
		33	ሪፍት ቫሊ ዩኒቨርስቲ	ጅማ	28	
		34	አሰላ መምህራን ኮሌጅ	አሰላ	15	
		35	ጭላሎ ኮሌጅ	አሰላ	15	
		36	ጅማ ቴ/ሙ ኮሌጅ	ጅማ	15	
		37	ጅማ የመንስት 1ኛ ደ/ት/ቤት	ጅማ	4	
		38	አሰላ የመንግስት 1ኛ ደ/ት/ቤት	አሰላ	4	
		39	አዳማ የመንግስት 1ኛ ደ/ት/ቤት	አዳማ	4	
		40	ጅማ የግል 1ኛ ደ/ት/ቤት	ጅማ	4	
		41	አሰላ የግል 1ኛ ደ/ት/ቤት	አሰላ	4	
		42	አዳማ የግል 1ኛ ደ/ት/ቤት	አዳማ	4	
		43	ጅማ የመንስት 2ኛ ደ/ት/ቤት	ጅማ	4	
		44	አሰላ የመንግስት 2ኛ ደ/ት/ቤት	አሰላ	4	
		45	አዳማ የመንግስት 2ኛ ደ/ት/ቤት	አዳማ	4	
		46	ጅማ የግል 2ኛ ደ/ት/ቤት	ጅማ	4	

		47	አሰላ የግል 2ኛ ደ/ት/ቤት	አሰላ	4	
		48	አዳማ የግል 2ኛ ደ/ት/ቤት	አዳማ	4	
		49	ደቡብ ቴ/ሙ/ት/ስ ቢሮ	አዋሳ	24	
		50	ጋሞ ዞን ቴ/ሙ/ት/ስ መምሪያ	አርባምንጭ	6	
		51	ጉራጌ ዞን ቴ/ሙ/ት/ስ መምሪያ	ወልቂጤ	5	
		52	ወላይታ ዞን ቴ/ሙ/ት/ስ መምሪያ	ሶዶ	5	
		53	ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ	ወልቂጤ	49	
		54	ቅድስተ ማሪያም ዩኒቨርስቲ	አርባምንጭ	17	
		55	አርባምንጭ መምህራን ኮሌጅ	አርባምንጭ	15	
		57	አሊያንስ ኮሌጅ	አርባምንጭ	9	
		58	ዱራሜ ቴ/ሙ ኮሌጅ	ዱራሜ	15	
		59	አርባምንጭ የመንግስት 1ኛ ደ/ት/ቤት	አርባምንጭ	6	
		60	ወልቂጤ የመንግስት 1ኛ ደ/ት/ቤት	ወልቂጤ	4	
		61	ወላይታ የመንግስት 1ኛ ደ/ት/ቤት	ሶዶ	4	
		62	አርባምንጭ የግል 1ኛ ደ/ት/ቤት	አርባምንጭ	4	
		63	ወልቂጤ የግል 1ኛ ደ/ት/ቤት	ወልቂጤ	4	
		64	ወላይታ የግል 1ኛ ደ/ት/ቤት	ሶዶ	4	
		65	አርባምንጭ የመንግስት 2ኛ ደ/ት/ቤት	አርባምንጭ	8	
		66	ወልቂጤ የመንግስት 2ኛ ደ/ት/ቤት	ወልቂጤ	4	
		67	ወላይታ የመንግስት 2ኛ ደ/ት/ቤት	ሶዶ	4	
		68	አርባምንጭ የግል 2ኛ ደ/ት/ቤት	አርባምንጭ	4	
		69	ወልቂጤ የግል 2ኛ ደ/ት/ቤት	ወልቂጤ	4	
		70	ወላይታ የግል 2ኛ ደ/ት/ቤት	ሶዶ	4	
	ድምር				914	

ሰንጠረዥ ለ፡ የሙስና ስጋት ደረጃ ማትሪክስ/Corruption Risk Prioritization Matrix

የሙስና ስጋት የመከሰት ዕድል	ከፍተኛ	መካከለኛ	ከባድ	ከባድ
	መካከለኛ	አነስተኛ	መካከለኛ	ከባድ
	ዝቅተኛ	አነስተኛ	አነስተኛ	መካከለኛ
		አነስተኛ	መጠነኛ	ከባድ
		የተጽዕኖ ደረጃ		